አዲስ ዘመን
እናድ
ረቡዕ
82ኛ ዓመት ቁጥር 060 ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ







# የአርቲስት አሊ ቢራ የቀብር ሥነሥርዓት በድሬዳዋ ከተማ ተፈጸመ

**ሞገስ ጸጋዬ**

ድሬዳዋ፡- የክቡር አርቲስት አሊ ቢራ የቀብር ሥነሥርዓት በድሬዳዋ ከተማ በርካታ ሕዝብ፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎችና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ተፈጸመ። የአርቲስቱ የቀብር ሥነሥርዓት ከመፈጸሙ በፊትም በአዲስ አበባና በትውልድ ስፍራው ድሬዳዋ የተለያዩ የሶላትና የሽኝት መርሃግብሮች ተከናውነዋል፡፡

የድሬዳዋው የሽኝት መርሃግብር ላይ ንግግር ያደረጉት የከተማዋ ከንቲባ አቶ ጁሀር ከድር እንደገለጹት፤ አርቲስት አሊ ቢራ ለሕዝብ ነፃነት እኩልነት በመታገል በጐ ተጽእኖ ማምጣት የቻለ አርቲስት ነበር። ሕይወቱ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ የሠራቸው ሥራዎች አንድነትን የሚያጠናክሩና የሚያወድሱ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና የነበረው አርቲስት አሊ ቢራ በሞት ሲለየን የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ኀዘን ተሰምቶናል ሲሉ ኀዘናቸውን ገልጸዋል።

የድሬዳዋ ፈርጥ አሊ ቢራ በምድር እስካለ ድረስ ለሰዎች አንድነት በሙዚቃው ሠርቷል፣ በሥራውም

የአርቲስት አሊ ቢራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በሽሬ፣በራያና በአክሱም አካባቢዎች ከ342 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የምግብ እርዳታ ቀርቧል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሽሬ፣ በራያ ባላ፣ በራያ አለማጣ፣ በግደም፣ በኮረም፣ በአክሱምና በሽራሮ አካባቢዎች ከ342 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው የምግብ እርዳታ ማቅረቡን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ

በሽሬ፣ በራያና በአክሱም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሰላም ውይይቱን መቃወም ውጤት አያመጣም

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ አባላት ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ስሜት የደቡብ አፍሪካውን የሰላም ውይይት የተቃወሙበት መንገድ ውጤት የሚያስገኝ አይደለም ሲሉ የሕግና ፖለቲካ ምሁሩ ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ ተናገሩ።

ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰላም ውይይቱን በተቃረነ መንገድ የቆሙ አካላት ዓላማቸው ሰላም እንዳይመጣ በመሆኑ ጥረታቸው ውጤት እንደማያመጣ ማወቅ ይገባል።

የሰላም ውይይቱን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ



# «አፍሪካ የተፈጥሮ ሀብቷን ተጠቅማ እንድትበለጽግ መሠረተ ልማቶቿን ማሳደግ ይገባል»

\- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ ያላትን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅማ እንድትበለጽግ መሠረተ ልማቶቿን ማስተሳሰርና ማሳደግ እንደሚገባ ፕሬዚዳት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

ለአራት ቀናት የሚቆየው 8ኛው የአፍሪካ የመሐንዲሶች ሳምንትና 6ኛው ኮንፈረንስ «ተደጋጋፊና የተሳለጠ መሠረተ ልማት በአፍሪካ» በሚል መሪሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም ትናንት ተጀምሯል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በመክፈቻው ሥነሥርዓት ላይ እንደገለጹት፤ መሠረተ ልማትን ማሳደግ አህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ለመፍጠር ወሳኝ ሚና አለው።

«አፍሪካ የተፈጥሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ከስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎች የሚሠሩበትን መንገድ የሚጠቁም መመሪያ እየተዘጋጀ ነው

ገጽ 3

# ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትንና የኢቢሲን የቦርድ አባላት ሹመት መርምሮ አፀደቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትንና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን የቦርድ አመራሮች ሹመት መርምሮ አፀደቀ።

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለተኛ ዓመት የሥራ ዘመን ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባውን ትናንትና ሲያደርግ በዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) የቀረቡትን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት (ኢፕድ) እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ)ን የቦርድ አባላትና አመራሮች ሹመት ምርምሮ አጽድቋል።

የዕጩ ቦርድ አመራር አባላቱን ዝርዝርና የትምህርት ደረጃ እንዲሁም የሥራ ልምድ ያቀረቡት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ ቤልጅጌ ዕጩዎቹ የተመለመሉበትን መሥፈርት ለምክር ቤቱ አስደምጠዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ ለእያንዳንዱ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የቦርድ አባላት መረጣ ብዝኃነት፣ ዕውቀት፣ የሥራ ልምድንን ያገናዘበ ነው። በዋናነት ወጣቶችና ሴቶችን ያካተተ ከመሆኑ ባለፈ ተቋማቱን ለመደገፍ ያላቸውን ዝግጁነትን መሠረት በማድረግ ምልመላው መከናወኑን ለምክር ቤቱ ተናግረዋል።

በዚህም መሠረት የአፍሪካ የልሕቀት አካዳሚ አመራር የሆኑት ዶክተር ምህረት ደበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢነት መቅረባቸውን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ አባላት እንዲሆኑ ደግሞ ዶክተር ምህረት ደበበ ሙሃዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንዔል ክብረት፤ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ፣ አቶ ማዕረጉ በዛብህ፤ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ፤ ወይዘሮ ሐና አርዓያሥላሴ፣ ረዳት ፕሮፌሰር መኩሪያ መካሻ፣ ወይዘሮ ነብሃ መሀመድና ዶክተር ካይረዲን ተዘራ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመልምለው መቅረባቸውን አቶ ተስፋዬ ጠቁመዋል።




የምክር ቤቱ አባላት የቀረቡት ዕጩዎች የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን አሠራርና የሚዲያ ሥራዎች ለማሳደግ የሚረዱ መሆናቸውን አቶ ተስፋዬ ገልጸው፤ አብዛኞቹ ለብዙኃን መገናኛ ሥራ ቅርበት ያላቸውና የካበተ የሥራ ልምድ ያላቸው መሆኑን አብራርተዋል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቦርድ አባላቱን ሹመት የውሳኔ ቁጥር 3/2015 አድርጎ በአብላጫ ድምጽ አፅድቋል።

ምክር ቤቱ በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ አባላትንም ሹመትንም ምርምሮ አፅድቋል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አቅራቢነት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ ሰብሳቢ እንዲሆኑ የተመለመሉት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ዶክተር ለገሰ ቱሉ መሆናቸውን አቶ ተስፋዬ አስታውቀዋል። በተጨማሪ ዶክተር አብዱልዋሳ አብዱላህ፣ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ፣ አቶ ጃፋር በድሩና አቶ መሳፍንት ተፈራ፣ ዶክተር ንጉሴ ተፈራ፣ አቶ የሱፍ ኢብራሂም፣ ወይዘሮ አመለወርቅ ሕዝቅኤልና ፕሮፌሰር ሚና አቡበከር የኢቢሲ የቦርድ አባላት ሆነው መቅረባቸውን አቶ ተስፋዬ ገልጸዋል። ምክር ቤቱም የኢቢሲን የቦርድ አባላት ሹመት ውሳኔ ቁጥር 2/2015 በማድረግ በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል።


አቶ ሙሉጌታ አያሌው

# ኮሚሽኑ በሩብ ዓመቱ ለ202 የግብር ይግባኝ መዝገቦች ውሳኔ ሰጠ

**በኃይሉ አበራ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በ2015 በጀት ዓመት ባለፉት ሦስት ወራት የአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ገንዘብ ጉዳይ ባለባቸው 202 የግብር ይግባኝ መዝገቦች ላይ ውሳኔ መስጠቱን የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አስታወቀ።

የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት አቶ ሙሉጌታ አያሌው የ2015 በጀት ዓመት ሩብ ዓመት የእቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ኮሚሽኑ በ2015 በጀት ዓመት ባለፉት ሦስት ወራት የአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ገንዘብ ጉዳይ ያለባቸው የ202 የግብር ይግባኝ መዝገቦች ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ኮሚሽኑ የግብር ይግባኝ ውሳኔ የሰጣቸው 202 መዝገቦች ውስጥ 128 መዝገቦች የገቢዎች ሲሆኑ 74ቱ ደግሞ ከጉምሩክ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

ከገቢዎች የቀረቡት 128 መዝገቦች 404 ሚሊዮን 808 ሺህ ብር የሚመለከቱ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልጸው፣ ከጉምሩክ የቀረቡት 74 መዝገቦች 865 ሚሊዮን ሲሆን በድምሩ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ገንዘብ የያዙ መዝገቦቹ ውሳኔ ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

ተቋሙ በሩብ ዓመቱ ሙሉ በሙሉ እቅዱን ማሳካት መቻሉን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ፈጣን፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው አሠራር የመዘርጋቱ ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

ከ202 መዝገቦች ውስጥ 132 ሰዎች ይግባኝ አመልክተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ተመልክቶ 11 መዝገቦችን እንደገና ታይተው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለኮሚሽኑ መመለሱንም ጠቁመው፤ እነዚህም በሚቀጥለው ሩብ ዓመት የሚታዩ ናቸው ብለዋል።

የኮሚሽኑ ዋና ሥራ የታክስ ቅሬታዎችን እየተመለከተ ውሳኔ መስጠት መሆኑን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ በ2014 በጀት ዓመት ውሳኔ ሳያገኙ የዞሩ 354 መዝገቦች፣ አዲስ የተከፈቱ 147 መዝገቦች በድምሩ 501 መዝገቦች እንደቀረቡ አውስተዋል።

ከእነዚህም መዝገቦች ውስጥ 55ቱ ለመልስ፣ 242ቱ ለቃል ክርክር፣ ሁለቱ ለብይን ተቀጥረው ቀሪዎቹ 202 መዝገቦች ደግሞ ለውሳኔ መቀጠራቸውን አብራርተዋል።

ክርክር ላይ ያለ ገንዘብ በቆየ ቁጥር ለመንግሥትና ለንግዱ ማህበረሰብም ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ውሳኔዎቹ በወቅቱ ተፈጻሚ ሊሆኑ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍና ተደራሽ ለማድረግ ኤክሶካ ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር ከሰኔ ወር ጀምሮ ሥራ ላይ ባዋለው መተግበሪያ በመጠቀም የዳታ ቤዝ ማዕከል ማቋቋሙንም ተናግረዋል። ከ120 መዝገቦች በላይ በኦንላይን መመዝገቡንም ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ አንድ ሺህ 385 መዝገቦችን ዲጂታላይዝ ማድረጉንም የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ ከገቢዎች እና ከጉምሩክ ጋር በቅርበት መሥራት መቻሉ የተሻለ ውጤት ማስገኘቱንም አመላክተዋል።

የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ ባለፈው በጀት ዓመት ዳኞች ዓመት ፈቃዳቸውን ሳይወጡ በመሥራታቸው በ715 ውዝፍ መዝገቦች ላይ ውሳኔ መስጠት መቻሉንና እነዚህ ውሳኔ ያገኙ መዝገቦች የአራት ቢሊዮን 374 ሚሊዮን 978 ሺህ ብር ጉዳዮችን የያዙ መሆናቸውን አስታውሰዋል።

# ኢትዮ- ኬንያ የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር የሙከራ ሥራ በስኬት ተከናወነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በኢትዮ- ኬንያ የኮንቨርተር ስቴሽንና የማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክት ላይ ኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ የሙከራ ሥራ በስኬት መካሄዱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡

የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጁ አቶ ቴዎድሮስ አያሌው እንገደለፁት፤ በኢትዮ ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክት ላይ ኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ የሙከራ ሥራ ትናንት በይፋ ተጀምሯል፡፡

በፕሮጀክቱ ላይ የተተከሉ የተለያዩ የኤሌክትሮ ሜካኒካል መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን እንዲሁም የኮሙዩኒኬሽን ዳታ ሲግናሉን በተለያየ ጊዜ የመፈተሽ እና የመሞከር ሥራ ሲሠራ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ቴዎድሮስ፣ በዛሬው ዕለት ደግሞ ኃይል በማስተላለፍ (energize በማድረግ) ከኬንያ ጋር ያለውን ግንኙነት ያለምንም ችግር መሞከር ተችሏል ብለዋል፡፡

የሙከራ ሥራው መሳካቱ በቅርቡ ከኬንያ ጋር የሚጀመረው የኃይል ትስስር ሥራ በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚከናወን አመላካች መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከቀናት በፊት የኮሙዩኒኬሽን ሲግናል በመላክ ሲግናሉን ከኬንያ ኔትወርክ ጋር ማገናኘት መቻሉን አቶ ቴዎድሮስ ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ኃይል ማስተላለፍ ሲጀምር በኅብረተሰቡ ላይ አደጋ እንዳያደርስ መስመሩ ከሚያልፉባቸው ዞኖች በየደረጃው ከሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ከወረዳና ከቀበሌ ተወካዮች ጋር የውይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች መካሄዳቸውን አስታውሰዋል፡፡

በተሠራው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ምክንያት የሙከራ ሥራ እየተከናወነ ባለበት ወቅት ምንም አደጋ አለማድረሱንም አቶ ቴዎድሮስ አረጋግጠዋል፡፡



የኢትዮ- ኬንያ የማስተላለፊያ መስመርና ኮንቨርተር ስቴሽን ፕሮጀክት በ334 ነጥብ 5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 214 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላሩ ለኮንቨርተር ስቴሽኑና ለግራውንድ ኤሌክትሮድ መስመር የግንባታ ሥራ እንዲሁም 120 ሚሊዮን ዶላሩ ደግሞ ለማስተላለፊያ መስመሩ የዋለ ነው፡፡

የግንባታ ሥራው በ2008 የተጀመረው ይህ ፕሮጀክት እስከ 2000 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ አቅም እንዳለው በፕሮጀክቱ ሲነየር ፕሮጀክት ኢንጂነር ኃይለማርያም ሞገስ ገልፀዋል፡፡

የማስተላለፊያ መስመሩ የግንባታ ሥራ እንደ አውሮፓውያኖች አቆጣጠር በ2018 እንዲሁም የኮንቨርተር ስቴሽኑ በታኅሣሥ 2021 እ.ኤ.አ መጠናቀቁን ኃይለማርያም ጠቁመዋል፡፡

ይሁን እንጂ የፕሮጀክቱ አካል የሆነውና በኬንያ በኩል ሲገነባ የነበረው በወቅቱ መጠናቀቅ ባለመቻሉ ኢነርጃይዝ ሳይደረግ ቆይቷል፡፡

የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የማስተላለፊያ መስመር የግንባታ ሥራ “CET” በተሰኘ የቻይና ኩባንያ የተከናወነ ሲሆን የኮንቨርተር ስቴሽኑና የግራውንድ ኤሌክትሮድ መስመሩ ደግሞ ሲመንስ በተሰኘ ኩባንያ ተከናውኗል፡፡

በኢትዮጵያ በኩል በተገነባው የኢትዮ - ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክት ላይ 994 የመስመር ተሸካሚ ታወሮች የተተከሉ ሲሆን፣ 440 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የኃይል ማስተላለፊያ መስመርና የዳታ ሲግናል ማስተላለፊያ ኬብሎችም ተዘርግተውለታል።

# ከስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎች የሚሠሩበትን መንገድ የሚጠቁም መመሪያ እየተዘጋጀ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- መገናኛ ብዙኃን ከሰላም ስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን በምን መልኩ መሥራት እንዳለባቸው የሚጠቁም መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አስታወቀ።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ኢድሪስ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰላም ስምምነቱ ከተጠቀሱ ጉዳዮች አንዱ ስምምነቱን ከሚረብሹ ዘገባዎች መታቀብ የሚለው ይገኝበታል። እንዲሁም የሰላም ስምምነቱን ተከትለው የሚወጡ ዘገባዎችም በመልካም እይታና በሚገባቸው ልክ መዘገብ ይገባል። ከዚህ መነሻ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን ከሰላም ስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን በምን መልኩ መሥራት እንዳለባቸው የሚጠቁም፣ ለተቋማቱ አቅም የሚፈጥርና እንደ ማጣቀሻ ሊጠቀሙበት የሚችል መመሪያ በባለስልጣኑ እየተዘጋጀ ነው ብለዋል።

ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ለሰላም ሀሳቦች የሚጠቅም ስላልሆነ ሊገታ ይገባዋል ያሉት ዋና ዳይክተሩ፤ መመሪያው በሰላም ስምምነቱ የተቀመጠውን ግዴታ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። መመሪያውን መነሻ በማድረግም ባለስልጣኑ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸውን የሞራል፣ የሙያና ሕጋዊ ግዴታዎችን አክበረው እንዲሠሩ በየጊዜው የክትትልና ድጋፍ ሥራ በመሥራት የማስተካከልና



አቶ መሐመድ ኢድሪስ

ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲመጡ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

መመሪያው በዚህ ሳምንት ውስጥ ተጠናቆ መገናኛ ብዙኃን፣ ሕዝቡና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲያውቀው ይደረጋል ያሉት ኃላፊው፤ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን የሰላም ግንባታ ላይ የሚጠቅባቸውን ሚና እንዲወጡ የሚያግዝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የሰላም ጉዳይ የሕዘብ ጉዳይ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በሰላም መረጋገጥ ላይ መገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸው ሚና የማይተካ ስለሆነ ያላቸው ኃላፊነት ከሙያዊ ሥነምግባርና ከሞራልም ጭምር የሚመነጭ መሆን እንዳለበት አመልክተዋል።

የመገናኛ ብዙኃን ሚና የሰላም ስምምነቱ ተሳካቶ ወደ ልማት ለመግባትና ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲያገግሙ ለማገዝ ምን አወንታዊ ሚና ልጫወት ከሚል እሳቤ የሚመነጭ መሆን ይኖርበታል ብለዋል።

መገናኛ ብዙኃን የሰላም ስምምነቱ ወደ መሬት ወርዶ ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን በኃላፊነት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ስምምነቱን ከአውዱ ውጪ ባለመተርጎምና አገሪቱ ላይ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ እንዲቀየር የሚያግዝ ሥራ ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

እያንዳንዱ የመገናኛ ብዙኃን ተቋም የተጎዱት እንዲበረቱና የማኅበረሰቡ የርስ በርስ መስተጋብር እንዲጠናከር በማድረግ የሰላም ስምምነቱ ከግብ እንዲደርስ የሚጠበቅባቸውን አዎንታዊ ሚና መጫወት እንዳለባቸውም መልዕክት አስተላልፈዋል።

---



## «የሰላም ስምምነቱ የሕዝብን ስቃይ የሚያስወግድና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን የሚያረጋግጥ ነው»

\- የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ)

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ:- በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት የሕዝብን ስቃይ የሚያስወግድ፣ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን ያረጋገጠ በመሆኑ በአዎንታና በደስታ እንደሚቀበለው ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) አስታወቀ። ስምምነቱን የሚያጣጥሉ አንዳንድ ግለሰቦችና ተላላኪዎቻቸው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡም አሳስቧል።

የፓርቲው ሊቀመንበር አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) የሰላም ስምምነቱን አስመልክቶ ትናንት በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በጦርነቱ የተጎዳው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን የትግራይ ሕዝብ ደግሞ በተለየ መልኩ የገፈቱ ቀማሽ ሆኗል። ስምምነቱ በሁለት ተከታታይ ዓመታት በሕዝቡ ላይ ሲያደርስ የነበረውን ስቃይ በማስቀረት የትግራይና የአጎራባች ክልሎች መልካም ጉርብትናን የሚፈጥርና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን ያረጋገጠ ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡

ስምምነቱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የበላይ ኃይል መሆኑ የታመነበት ክስተት መሆኑን ያነሱት አረጋዊ(ዶ/ር)፤ ለችግሮቻችን አፍሪካዊ መፍትሔ መገኘቱ ሁሉንም የሚያኮራ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአንጻሩ የሕዝቡ ሰላም፣ አብሮነትና ተደጋግፎ ማደጉን የማይፈልጉ የጦርነት ነጋዴዎች እና ግብረአበሮቻቸው ስምምነቱን እያጣጣሉ መሆናቸውን የጠቆሙት ሊቀመንበሩ፤ በተለይ የትግራይ ሕዝብ እየደማ መኖር ስለሌለበት ሰላሙን የመጠበቅ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

እነዚህ ስግብግብነት የተጠናወታቸው የፖለቲካ ነጋዴዎች በመሆናቸው የትግራይ ሕዝብ ስቃይና መከራ ግዳቸው አይደለም ያሉት አረጋዊ(ዶ/ር)፤ ሰላም ፈላጊው ሕዝብ መሰሪ አቋማቸውን እየኮነነ፣ ክፉ ድርጊታቸውን እያጋለጠ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት ማዞር እንደሚኖርበት አስታውቀዋል፡፡

የራሳችን ችግር በራሳችን መፍታት ያልጣማቸው እና የሕዝቡ ስቃይና መከራ የማይሰማቸው የተወሰኑ የውጭ ኃይሎች ስምምነቱን አቅጣጫ ለማሳት የሚያደርጉት ጥረት መኖሩን የጠቀሰው መግለጫው፤ ከጣልቃ ገብነት እንቅስቃሴያቸው እንዲታቀቡ ጠይቋል፡፡

ትዴፓ የሰላም ስምምነቱ እውን እንዲሆን የደከሙትን ወገኖች ማለትም የአፍሪካ ሕብረት፣ ኢጋድ፣ የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ሁሩሩ ኬንያታ እና የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሴጎን ኦባሳንጆን ያመሰግናል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ አሁን ላይ ለሁሉም የሚያወጣውና ጠቃሚው ብቸኛ አማራጭ ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

---

## ስንዴ ወደ ውጭ ለመላክ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ደረጃውን የጠበቀ ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ ከላኪዎች ጋር ትናንት ውይይት ሲያደርጉ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የእርዳታ ስንዴ ከማስገባት አልፋ ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ቅድመ ዝግጅት እያደረገች ነው፡፡

ወደ ውጭ የሚላከው ስንዴ ከአገር ውስጥ ፍጆታ የተረፈ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ ለዚሁ ይረዳ ዘንድ በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የንግድ ሥርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ በበኩላቸው፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ የጥራት ጉዳይ ለድርድር መቅረብ እንደሌለበትና ላኪዎችም ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

ላኪዎችም በፊት ኢትዮጵያ የነበራት ገጽታ ተቀይሮ ከስንዴ አስመጪነት ወደ ላኪነት መሸጋገሯ የአገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት መልካም አጋጣሚ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የተጣለባቸውን አገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ እንደሆኑ መጠቆማቸውን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

ባለፈው ዓመትም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 24 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ መገኘቱን የሚገልጹት የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን፤ ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት በበጋ ስንዴ ልማት ለተገኘው አመርቂ ውጤትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት ፣ የተቀናጀ የፋይናንስ ድጋፍና አገራዊ የስንዴ የመስኖ ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽሕፈት ቤት መዘርጋቱ ከፍተኛ ሚና ማበርከቱን አገራዊ የበጋ ስንዴ ልማት በሶማሌ ክልል ይፋ በሆነበት ወቅት ጠቁመው ነበር።

ሚኒስትሩ በዚሁ ወቅት፤ በ2015ዓ.ም የበጋ መስኖ ስንዴ ፕሮግራም ከተነሳበት ከውጭ የሚገባን ስንዴ በአገር ውስጥ መተካት፤ የሥራ ዕድል መፍጠርና በቂ ምርት ለግብርና ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ ማቅረብን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግም ታሳቢ አድርጓል ብለዋል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ዘንድሮ በበጋ ስንዴ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ዕቅድ ተይዟል። ይህም የአገርን ፍጆታ ሙሉ ለሙሉ ከማሟላት ባለፈ ለውጭ ንግድ ማቅረብ እንደሚያስችል ያስረዳሉ።

አገራዊ ዓመታዊ የስንዴ ምርት ፍላጎት 107 ሚሊዮን ኩንታል የሚደርስ ሲሆን፣ በክልሎች መረጃ መሠረት ከዘንድሮው የመኸር ምርት ዘመን 101 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት ፤ ከበጋ ስንዴ ልማት ጋር ሲደመር 153 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህም ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ትርፍ ምርት ይኖራል፡፡ ይህ ደግሞ የአገር ውስጥ ፍጆታን ሙሉ ለሙሉ ከማሟላት ባለፈ ለውጭ ንግድ ለማቅረብ ያስችላል ነው ያሉት፡፡

በመስኖ ከሚለማውን 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት ውስጥ ቢያንስ 26 ሚሊዮን ኩንታሉን ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል ትርፍ ምርት መኖሩንም ጠቅሰዋል፡፡

# የአርቲስት አሊ ቢራ የቀብር ሥነሥርዓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከ260 በላይ ዜማዎቹን ትቶልን አልፏል። ከዚህ በኋላ ትቶልን በሄደው ሥራዎች ልንማር ይገባል ብለዋል።

ድሬዳዋ ዘወትር ከአሊ ቢራ ጋር ትነሳለች፣ በሙዚቃው እንድትታወቅም አድርጓል ሲሉ ከንቲባው ተናግረዋል።

የሐረሪ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ኦርዲን በድሪ በበኩላቸው፤ አገራችን ትልቅ ሰው አጥታለች፣ አሊ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኩራትና ምልክት ነበር ሲሉ ኀዘናቸውን ገልጸዋል።

የሰላምና የፍቅር ሰው ነበር፣ በኖረበት ጊዜ ለአንድነት ከፍተኛ ሥራን ሠርቷል። በብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች መካከል መተሳሰብ እንዲኖር ያደረገው ጥረት የማይረሳ ነው ብለዋል።

የሶማሌ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኢብራሂም ኡስማን አርቲስት አሊ ቢራ ከድምፃዊነት ባሻገር የሙዚቃ ሊቅ ነበር፤ በርካታ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጫወትም ለረጅም ዓመታት በዘርፉ ሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል። የአፋን ኦሮሞ የዘመናዊ ሙዚቃ አባት ነው፣ ይህንንም በራሱ ጥረት ያገኘው ነው። የምሥራቅ ኢትዮጵያ በተለይ የድሬዳዋ ልዩ ምልክት ነበር ብለዋል። ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጆችና ለአድናቂዎች እንዲሁም ለመላ ኢትዮጵያውያን መጽናናት ተመኝተዋል።

የአርቲስት አሊ ቢራ ባለቤት ወይዘሮ ሊሊ ማርቆስም በሥነሥርዓቱ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት አሊ በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው አርቲስት መሆኑን ማየት ችያለሁ ብለዋል። መላ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለባለቤታቸው ላሳየው ፍቅር እና በቀብሩ ላይ ለተደረገው ደማቅ ሥነሥርዓት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



በአርቲስት አሊ ቢራ ሥርዓተ ቀብሩ ላይ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ፣ የሐረሪ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ኦርዲን በድሪን፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ጁሀር ከድር፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶችና በርካታ የድሬዳዋ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።

አርቲስት አሊ ቢራ ሥርዓተ ቀብሩ ከመፈጸሙ በፊት በጠዋቱ ክፍለጊዜ በአዲስ አበባ ወዳጅነት አደባባይ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ አባገዳዎች፣ የእምነት አባቶች፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎችና የአርቲስቱ አድናቂዎች በተገኙበት የሽኝት መርሃግብር መከናወኑ ይታወሳል።

በሽኝት መርሃግብሩም ላይ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፣ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሙያ ማህበራት ኃላፊዎችና የሙያ አጋሮች እንዲሁም የአርቲስት አሊ ቢራ የቅርብ ወዳጆች ንግግር አድርገዋል።

አርቲስት አሊ ቢራ በ1941 ዓ.ም የተወለደ ሲሆን፣ ከ60 ዓመት በላይ በሙዚቃ ዓለም ያገለገለ አንጋፋ የኪነጥበብ ሰው ነበረ።

# የሰላም ውይይቱን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት በፈረሙት የሰላም ስምምነቱ ላይ አሁን ተቃውሞ የሚያነሱ አካላት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የግል ፍላጎታቸውን ብቻ የሚያራምዱ ሊሆኑ እንደሚችል መገመት ይቻላል ብለዋል።

በተጨማሪ በውጭ አገራት ሆነው የሰላም ስምምነቱን በጭፍን የሚቃወሙ አካላት እንዳሉም ማወቅ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር ጥላሁን፤ ያም ሆነ ይህ ግን ዋናው ጉዳይ የሚወሰነው አገር ውስጥ ባለው ሁናቴ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተሳሳተ መንገድ የሰላም ውይይቱን ስምምነት ተፈጻሚ እንዳይሆን ተቃውሞ የሚያሰሙ አካላት ራሳቸውን ከመከፋፈል ውጪ ተጨባጭ ውጤት የማያስገኝ መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል ብለዋል።

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በዋነኛነት ጉዳት የደረሰበት አገር ውስጥ ያለው ሕዝብ መሆኑን አንዳንድ የዳያስፖራ አባላት መዘንጋት እንደሌለባቸውም ፕሮፌሰር ጥላሁን ገልጸዋል።

እነዚህ አካላት በሰላም ውይይቱ ላይ ተቃውሞ ሲያነሱ በዋናነት አገር ውስጥ ያለውንና ሰላም የሚፈልገውን ሕዝብ ታሳቢ ያደረገ አካሄድ ሊኖራቸው ይገባል ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ጥላሁን ገለጻ፤ አሁን ላይ አገር ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ተቀይሯል። ጦርነቱን ለማቆምና የሰላም ስምምነቱን ተፈጻሚ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች ተጀምረዋል።

ሕዝቡም ፍላጎቱ ሰላም መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ስምምነቱ ሊፈጸም አይገባም ብሎ መቃወም ተገቢ አይደለም ፤ በሕዝብ ቁስል እንጨት ብከትበት አያምም እንደማለት ይቆጠራልም ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህ የተነሳ አሁንም የተወሰኑ የዳያስፖራ አባላይ የሰላም ስምምነቱን ሊቃወሙ ቢነሱም የሚገርም እንዳልሆነ ጠቁመዋል። ይሁንና የእነሱ ተቃውሞ ብቻውን የሰላም ሂደቱን ሊያስተጓጉል እንደማይችል ታውቆ ስምምነቱን በተገቢው መንገድ ማስፈጸም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር ጥላሁን እንዳስታወቁት የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ ሃሳቦች ላይ ሳይሆን ገንቢ ነገሮች ላይ በማተኮር የስምምነቱን ቀሪ ሥራዎች ማከናወን ይገባል።

# «አፍሪካ የተፈጥሮ ሀብቷን ተጠቅማ እንድትበለጽግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አፍሪካ ባላት እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ልክ እንድታድግ በአህጉሪቷ ያለው የመንገድ፣ የአየር ትራንስፖርትና ተያያዥ መሠረተ ልማቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ፕሬዚዳንቷ እንዳስታወቁት፤ በአፍሪካ የሲቪል ምህንድስናው ዘርፍ የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው የመሠረተ ልማት ግንባታ ፍላጎት ነው። አፍሪካም በዘርፉ ሙያ ያላቸውና ቴክኒካዊ ብቃታቸው የጎለበቱ ብቁ መሐንዲሶች በብዛት ያስፈልጓታል።

የመሠረተ ልማት ፍላጎትና አቅርቦት በፍጥነት እያደገ በመሆኑ ከፍላጎቱ ጋር የሚጣጣም ሥራ ማከናወን ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ለዚህም በምህንድስናው ሙያ የሚሳተፉ አፍሪካውያን ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

አፍሪካ መልማትና መበልጸግ የሚያስችላት የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራትም ተባብሮ መሥራት አለመቻል ትልቅ ፈተና ሆኖ እንደቆየባት የጠቆሙት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ አህጉሪቱ ያላትን ተፈጥሯዊ ሀብት መጠቀም ትችል ዘንድ በአፍሪካውያን መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነት መጠናከር አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

ለዚህ ደግሞ ወሳኝ በሆነው የመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ አፍሪካን በጋራ መገንባት እንደሚያስፈልግ ፕሬዚዳንቷ ተናግረዋል።

የአህጉራችን ሕዝብ ኑሮ ለመለወጥ እጅ ለእጅ ተያይዘን መሥራት አለብን ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ ለዚህም ዕድሉና አጋጣሚው በእጃችን ስለሆነ ዘመናዊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ተጠቃሚነታችንን ልናፋጥን ይገባል ብለዋል።

ባለን የማዕድን፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ የትራንስፖርት አማራጭና የግብርና ምርት ለመበልጸግና ከድህነት ለመውጣት መሠረተ ልማት ወሳኝ ነው። በመሆኑም ከኢንቨስትመንትና ሥራ ዕድል ፈጠራው ጎን የምህንድስናውን ዘርፍ ለማሳደግ ዓይነተኛ ትኩረት መስጠት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የአፍሪካ የመሐንዲሶች ማህበር ፕሬዚዳንት ካርሊን ዶርካስ በበኩላቸው፤ በትብብር ቀጣይነት ያለው የመሠረተ ልማት ዕድገት በጋራ መገንባት ይገባል። ለዚህም የአፍሪካ መሐንዲሶች ጉባኤ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ለአፍሪካ አስፈላጊው ቀጣናዊ ትስስር እንድታሳድግ በመሠረተ ልማት ትስስሩን ማጠናከር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የአፍሪካ የምህንድስና ጉባኤ የምሁራንን አቅም ለማስተባበር ዓይነተኛ መንገድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚና የኢትዮጵያ ሲቪል መሐንዲሶች ማህበር ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ዮናስ አያሌው እንዲሁም ከተለያዩ አገራት የመጡ የሲቪል መሐንዲሶች ማህበር አመራርና አባላት በጉባኤው እየተሳተፉ ይገኛል።

# በሽሬ፣በራያና በአክሱም አካባቢዎች ከ342 ሚሊዮን ብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ከጥቅምት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በሽሬ፣በራያ ባላ፣ በራያ አለማጣ፣ በግደም፣ በኮረም፣ በአክሱምና በሽራሮ አካባቢዎች ለሕዝቡ የምግብ ማለትም ስንዴ እንዲሁም አልሚ ምግብ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህንኑ አጠናክሮ በመቀጠል እስከ ጥቅምት 27 ቀን 2015ዓ.ም ብቻ በእነዚህ አካባቢዎች ሰብዓዊ ዕርዳታ ለሚፈልጉ ወገኖች 150 ሺህ 627 ነጥብ አምስት ኩንታል ስንዴና 14ሺህ 292 ኩንታል አልሚ ምግብ ተልኳል፡፡

በእነዚህ ስምንት ቀናትም ለ371 ሺህ 291 ወገኖች የስንዴ ድጋፍ እንደተደረገላቸው ገልጸው፤ ሕፃናት፣ ነፍሰ ጡሮች፣ አጥቢ እናቶችና አቅመ ደካሞች የሆኑ 952 ሺህ 798 ዜጎች ደግሞ የአልሚ ምግብ ድጋፍ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ ድጋፉ ለራያ ባላ፣ ለራያ አለማጣ፣ ለሽሬ፣ ለግደም፣ ለኮረም፣ ለአክሱምና ለሽራሮ ወገኖች የተደረገ ሲሆን፤ የተላከው ምግብና አልሚ ምግብ በገንዘብ ሲሰላ 342 ሚሊዮን 446ሺህ 800 ብር የሚያወጣ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ድጋፉ በአካባቢዎቹ ያለውን አስተዳደራዊ ሁኔታ በመጠቀም፤ በቀጣይም እነዚህ ወገኖች እንዲደገፉ የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡



ድጋፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት አቶ ደበበ፤ ሌሎች አካባቢዎችም አስተዳደራዊ ሁኔታው የበለጠ እየተጠናከረ ሲሄድ ተጎጂ ወገኖችን በመለየት ድጋፉ የሚቀጥል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎች በቅንጅት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ለዚህም በከፍተኛ አመራር የሚመራ ቡድን በየቦታው ጉብኝት እያደረገ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡ በጉብኝቱም ከኅብረተሰቡ ጋር ውይይት እየተደረገ እንዳለና በሚገኘው ውጤት መሠረት ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በአየርም ሆነ በየብስ ትራንስፖርት ለትግራይ ክልል ለዜጎች ሊደርስ የሚገባውን ጥሬ ገንዘብን ጨምሮ አስፈላጊ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ሲልክ ቆይቷል፡፡ በትግራይ ክልል ሰብዓዊ እርዳታ በተሳለጠ መንገድ እንዲደርስ በቂ ዝግጅት መደረጉን ለሰብዓዊ ድጋፍ የተዋቀረው ኮሚቴ መግለጹም ይታወቃል፡፡

የሰብአዊ ርዳታ አቅርቦትን ለማሳለጥ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ከአገር መከላከያ ሰራዊት፣ ከፌዴራል ፖሊስ እና ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መግባቱም ይታወቃል፡፡

የኮሚቴው ሰብሳቢ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በትግራይ አካባቢዎች ሰብዓዊ እርዳታውን በተሳለጠ መልኩ ለማድረስ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱንና ወደ ተግባር መግባቱንም በቅርቡ መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሕዝብ የሚቆረቆር ለሰላም ይሠራል!

በየትኛውም ዘመን የተገኘ ትውልድ ለተፈጠረበት ማኅበረሰብ ያለውን በጎ ሕሊና በተለያየ መንገድ ይገልጻል። ከሁሉም የተለመደው ግን የኀብረተሰቡን ነገዎች ከተስፋ በላይ የሚጨበጥ ለሚያደርገው ሰላም ምኞቱ ከፍ ያለ ነው።

ሰላም የአንድ ማኅበረሰብ ነገዎች /ተስፋዎች/ መሠረት ነው። ያለ ሰላም ነገን ቀርቶ ቀጣዮቹን ደቂቃዎች በተስፋ ለማሰብ መሞከር የሚታሰብ አይደለም። አስቦም እውን የሆነለት ማኅበረሰብ ስላለመኖሩ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል።

የሰላም ጉዳይ ከግለሰባዊ ስብዕና የሚመነጭ፣ እያደገ ሄዶ ማኅበረሰባዊ ማንነት ሆኖ የሚገለጽ፤ ለአንድ ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ዕድገት መሠረት የሆነ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ከዚህ የተነሳም የትኛውም ማኅበረሰብ ለሰላም ከፍያለ ትኩረት ይሰጣል።

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መገኛ ከመሆኗ አንጻር ስለ ሰላም ያለን ማኅበራዊ እሴቶች በቁጥርም በዓይነትም ብዙ ናቸው። ከዚህም የተነሳ የሰላም መውደዳችን ጉዳይ በበርካቶች የሚታወቅ ትልቁ እሴታችን ነው።

በርግጥም እንደ ሃገርና ሕዝብ ከዚህ ትልቅ እሴት የተነሳ በረጅሙ ዘመን ታሪካችን፤ ከሰላም ወዳድነታችን ውጪ፣ ድንበር ተሻግረን፣ ባህር አቋርጠን የተጓዝንበት ጥቁር ታሪክ ባለቤት አይደለንም። ለዚህ የሚሆንም የአስተሳሰብ ሆነ የሥነ ልቦና መሠረት የለንም።

በቅርቦቹ ዓመታት እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ ስማችን ጎልቶ ሲደመጥ የነበረው በሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች የመሳተፋችን እና ተልዕኮዎችን በስኬት ስለማጠናቀቃችን ነው። ያገኘናቸው እውቅናዎችም ስለ ሰላም ያለንን ቀናኢነት የኢትዮጵያውያንን ሰላም ፈላጊነት በተጨባጭ መናገር የቻለ ነው።

ይህ ማኅበራዊ እሴታችን በመሐከላችን ሊፈጠሩ ለሚችሉ አለመግባባቶችና ግጭቶች መፍቻ ዋነኛ አቅም እንደሚሆንና ሰላማችንንም አስጠብቆ ነገዎቻችንን ብሩህ ለማድረግ አልፋና ኦሜጋ እንደሆን ይታመናል።

እንኳን በአንድ ሃገር በሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ቀርቶ፤በአንድ ቤተሰብ መካከል አለመግባባቶች ሊፈጠሩ፤ አለመግባባቶቹ አድገው ወደ ግጭት ሊለወጡ ፤በግጭቱም የሚጠበቅና ከተጠበቀውም በላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል።

ችግሩ በራሱ የነገሮች ሁሉ መጨረሻ /ፍጻሜ/ ሊሆን አይችልም ፤ ሆኖም አያውቅም። ከዚያ ይልቅ ችግሩ ፍጻሜ የሚኖረው በአዲስ ጅማሬ ነው። ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ ወደ ፍጻሜው መጓዙ አይቀርም። ለተፈጥሯዊ ሂደቱ ትልቁ አቅም ግን ሰላምና የሰላም ሐዋሪያ ሆኖ መሰለፍ ብቻ ነው።

በሀገራችን እየሆነ ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም። የተፈጠሩ አለመግባባቶች ወደ ግጭት ተለውጠዋል፤ ግጭቶቹ ደግሞ ያልጠተበቁ ችግሮችን ፈጥረዋል። በችግሮቹም መላ ሕዝባችን ውድ ዋጋ ለመክፈል ተገድዷል።

እውነታው ግን የነገሮች ሁሉ ፍጻሜ የመሆን አቅም ስላልነበረው መሆን አልቻለም፤ከዚያ ይልቅ የሰላምና የእርቅ ጉዳይን ስቦ ማምጣት ችሏል። ይህ አዲስ ጅማሬ እንደ ሀገርና ሕዝብ እንድንቀጥልና ወደ ተፈጥሯዊ መንገዳችን እንድንመለስ የሚያስችል ትልቅ አቅም ሆኖ መጥቶልናል።

ይህ ዛሬ ላይ ብቻ ሳይሆን በቀደመው ረጅም ታሪካችን ውስጥ ደጋግሞ እየመጣ፤ እንደ ሃገር መቆም ያስቻለንና እንደ አንድ ቤተሰብ እንድንቀጥል ዕድል ፋንታ የሆነን ትልቁ ማኅበራዊ እሴታችን ነው።

ይህንን እውነታ ከጥላቻ ፤ ጥላቻ ከሚወልደው ስሜት ፤ስሜቱ ከሚፈጥረው መታወር ተወጥቶ በጠራ አዕምሮ፤ በሰከነ መንፈስ መመልከት ይገባል። ይህን ማድረግ ባለመቻል እንደግለሰብ ሆነ እንደ አንድ ማኅበረሰብ ክፍል ሊደርስብንም ሆነ ልናደርስ የምንችለውን ጥፋት ልንገራው ይገባል።

በተለይም በውጪ የሚኖሩ አንዳንድ የትግራይ ዲያስፖራ ኣባላት እየሄዱበት ያለውን የጥላቻ መንገድ ለማንም የማይበጅ መሆኑን ቆም ብሎ መመልከት ይገባል። ይህ የማይጠቅም መንገድ በዚህ የጥፋት መንገድ ውስጥ ላለው አካል ለራሱም ሆነ እቆረቆርለታለሁ ለሚለው የትግራይ ሕዝብ ሊያስገኝለት የሚችለው ምንም ጥቅም እንደሌለም በአግባቡ ሊያጤነው ይገባል።

በአውሮፓና አሜሪካ አደባባዮች እየወጣ ጦርነቱ መቆም የለበትም፤ የትግራይ ሕዝብ ለቀጣይ ጦርነት ራሱን ያዘጋጅ እያለ የሚያሰማው ጩኸት በጦርነቶች ብዙ ዋጋ እየከፈለ ላለ ሕዝብ ተቆርቋሪነት መገለጫ ሊሆን እንደማይችል ሊረዳው ይገባል።

የትግራይ ሕዝብ ከቀደሙት ጦርነቶች ያተረፈው አንዳች ነገር እንደሌለ፤ የትናንትም ፤የዛሬውም ሕይወቱ የሚናገረው ተጨባጭ እውነታ ነው። ይህን እውነታ በረሳ ማንነት የትግራይ ሕዝብ ተቆርቋሪ መሆን አይቻልም። ተቆርቋሪ ነኝ ብሎ አደባባዮችን ማጣበብም እንደሀገራችን አባባል "ያለ አዋቂ ሳሚ..."እንደሚባለው አይነት ነው። ፍጻሜውም ሳሚውንም ተሳሚውንም የማይጠቅም ያለአዋቂነት ነው!

---

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com
የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12
የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

---

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# የትግራይ ሕዝብ የሚሻው የሰላምና የልማት ሐዋሪያ እንጂ የጦርነት ሰባኪ አይደለም !

**ከመርደቂዮስ**

ለአንድ ሀገር ሕልውና ሆነ ለዜጎች ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ሰላም ዋነኛው ጉዳይ ነው። ከዚህ የተነሳም ሀገራትና መንግሥታት ስለሰላም አበክረው ይሠራሉ። በውጤቱም ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር ሰላምና መረጋጋት በማስፈን ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ልማትን ያጸናሉ ።

ይህንን ሀገራዊ እውነታ ዓለም አቀፍ ገጽታ ለማላበስ፤ ከዚያም በላይ ከሁከትና ከግጭት ነጻ የሆነች ዓለም ለመፍጠር ለዚህ የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማትን ከመመሥረት ጀምሮ ሰላምንና የሰላም ጉዳይን ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ በስፋት እየተሠራ ነው ።

ዓለም በቀደሙት ዘመናት ከጦርነትና ከግጭት ከሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት ውጪ ያተረፈችው አንዳች ነገር ባለመኖሩና ካለመደማመጥ እና ካልተገባ የአስተሳሰብ መሠረት የሚፈጠሩ ውድመቶችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ አቅሞችንም ለመገንባት ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ውጤቱ የታሰበውን ያህል ባይሆንም ዓለም ከቀደሙት ዘመናት የጦርነትና የግጭት ታሪኮች በመማር ስለ ሰላም የምታዜማቸው ዜማዎች አሁን ላይ በብዙ ተግዳሮቶች/ፈተናዎች ውስጥ ቢወድቁም የሰላም ድምጾች መሰማታቸውን አላቆሙም።

ዛሬም ስለሰላም የሚያዜሙ ድምጾች አሉ፤ ዛሬም ከጦርነትና ከግጭት ከሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት ውጪ የሚገኝ አንዳች ትሩፋት የለም የሚሉ ድምጾች አሉ፤ ዛሬም በጦርነትና በግጭት የሚገነባ ነገ እንደሌለ አበክረው የሚናገሩ ድምጾች አሉ።

በተለይም እንደኛ ባሉ ዛሬን አሸንፈው ለመውጣት በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ያሉ ሀገራትና ሕዝቦች በጦርነትና በግጭት ነገዎቻቸውን ከማጨለምና ትውልዶችን ተስፋ ቢስ ከማድረግ ባለፈ የሚያገኙት አንዳች ጠቀሜታ/ፋይዳ ሊኖር አይችልም ።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር ከውጪ ኃይሎች ጋር ካደረግናቸው የነጻነትና የሉዓላዊነት ጦርነቶች ውጪ በእርስ በርስ ጦርነት የከፈልነው ዋጋ እንዲህ በቀላሉ ተነግሮ የሚያበቃ አይደለም። እንደ ሕዝብ ከአቅማችንና ከፈቃዳችን በላይ ዋጋ ከፍለናል ።

ባለፉት የአጼዎች ዘመን ለአጼዎች ስምና ክብር እንደ ሀገር የከፈልነው ዋጋ አሁን ላላቸው ሀገራችን አሁናዊ እውነታ ትልቁ ምክንያት እንደሆነ ለማሰብ የሚከብድ አይደለም፤ ከዚህ የሚከፋው ግን እውነታው በዛሬው ሀገራዊ የፖለቲካ/ ኢኮኖሚ አስተሳሰባችን ላይ ያጠላው ጥላ ነው።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሀገሪቱ የተጀመሩ የለውጥ አስተሳሰቦችና አስተሳሰቦች የወለዱት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የግራና ቀኝ መንገደኝ ሆነው ሳይገጣጠሙ ቀርተዋል። ይህም ሀገርን እንደ ሀገር፤ ሕዝባችንን እንደ ሕዝብ ከፍያለ ዋጋ አስከፍለውታል።

ሕዝባችን በብዙ ተስፋ የሚያምጣቸው የለውጥ ምጦች በዚህ የትናንት ጥላ እየተጨናገፉበት፤ ነገዎቹን በአግባቡ መሥራት የሚችልበትን ተስፋና ከዚህ የሚመነጭ ራዕይ አይቶ በሙሉ ልብና ቁርጠኝነት መሄድ ሳይችል ቀርቷል።

ከሁሉም የሚያሳዝነው ከትናንት ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ ከሚኖርበት ማኅበረሰብ መማር ያልቻለው አንዳንድ ጽንፈኛ የትግራይ ዲያስፖራ ጉዳይ ነው። ስለ ሰላም ትልቅ ቦታ የሚሰጥ፤ በዚህም ሀገሩን ሀገር አድርጎ ጥገኝነት በሰጠው ማኅበረሰብ መሀል ሰላምን ተቃውሞ አደባባይ ካልሞላሁ የማለቱ እውነታ ነው።

የትግራይ ዲያስፖራ ትናንት በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ አደባባዮች "የሰላም ሐዋርያ" ሆኖ ሲጮህ፤ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል በአስቸኳይ ሰላም ይውረድ፤ ለዚህ ዓለም አቀፉ ኀብረተሰብ ጊዜ መስጠት የለበትም ሲል ተሰምቷል ።

ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ከመፈለግ ይመስል የነበረው የዲያስፖራው የአደባባይ ጩኸት፤ በሁለቱ አካላት መካከል የሰላም ስምምነት በተፈረመ ማግስት መልኩን ቀይሮ የሰላም ስምምነት ለምን አስፈለገ፤ ለትግራይ ሕዝብ ጦርነት ነው የሚሻለው ወደሚል ፍጹም የተቃረነ ጩኸት ተለውጧል።

በርግጥ ይህ ማኅበረሰብ የጦርነትን አስከፊነት ማሰብና መረዳት የሚያስችል ሰብዓዊ ማንነት አይኖረውም ብሎ ማሰብ ቀላል ሊሆን አይችልም፤ የትግራይን ምድር የደም ምድር/አኬልዳማ ያደረጉ ጦርነቶች የቱን ያህል የትግራይን ሕዝብ ዋጋ እንዳስከፈሉት የአደባባይ ሚስጥር ነው።

በነጻነት ስም ለ17 ዓመታት በተደረገው ጦርነት ከስድስት አስርት ሺህ በላይ የትግራይ ወጣቶች ለሞት ተዳርገዋል፤ በመቶ ሺዎች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል/ይህ ለአደባባይ የበቃ መረጃን ብቻ ያካተተ ነው። በዚህም በማኅበረሰቡ ላይ የደረሰውን የስነ ልቦና ጫና ለመናገርና ለመጻፍ የሚከብድ አይደለም።

በኢትዮ-ኤርትራም ጦርነትም ቢሆን ክልሉ የጦርነቱ አውድማ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በርግጠኝነት ከክልሉ ነዋሪዎች ይህን ያህል ቁጥር ያለው ነዋሪ ሞተ የሚል መረጃ ባይኖርም፤ ክልሉ የጦርነቱ አውድማ በመሆኑ ብቻ የትግራይን ሕዝብ ሊያስከፍል የሚችለው ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ስነልቦናዊ ዋጋ በቀላሉ የሚሰላ አይደለም።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በመንግሥትና በሕወሓት መካከል በተፈጠረው ግጭትም በአንድም ይሁን በሌላ የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ የግጭቱ ሰለባ ሆኗል። ለዚህ ሕዝብ ከሰላም ይልቅ ጦርነት መመኘት፤ ይህንንም በየአደባባዩ ያለ ሀፍረት ይዞ መጮህ የጤንነት አይመስልም።

በአንድ በኩል የትግራይ ሕዝብ ወገኔ ነው፤ ከኔ በላይ ሊቆረቆርለት የሚችል የለም የሚለው ይህ የትግራይ ዲያስፖራ፤ በሌላ በኩል የትግራይ ሕዝብ በየትኛውም መልኩ ከጦርነት ሊወጣ አይገባም፤ ልጆቹን፣ ጥሪቱንና ተስፋውን ለጦርነት መማገድ አለበት እያለ ነው።

ዛሬ ላይ ለትግራይ ሕዝብ ጦርነትን የሚመኝለት ይህ ዲያስፖራ፤ ከሀገር እንዴትና ለምን እንደወጣ፤ ከሀገር ውጪም እንዴት እንደሚኖር ማስታወስ ይጠበቅበታል። ባህር ተሻግሮ በብዙ መከራና ስቃይ አሁን ያለበት ሀገር እየኖረ ያለው ምን ተስፋ አድርጎ እንደሆነ በአግባቡ ሊያስተውል ይገባል ።

ይህ ዲያስፖራ ለትግራይ ሕዝብ ጦርነት ከመመኘቱ በፊት፤ ቀናትን አሸንፎ ከሀገር የተሰደደበትም ሕልሙን እውን ለማድረግ በቀን የቱን ያህል ሰዓት እንደሚሠራ፤ በዚህ እንኳን ሕልሙን ምን ያህል መግፋት እንደቻለ በአግባቡ ማጤን ይጠበቅበታል።

የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ነገ ላይ ሕልም ያለው ሕዝብ ነው፤ ይህ ሕልሙ በየትኛውም ሁኔታ በጦርነት እውን ሊሆኑ እንደማይችል ከትናንት ታሪኩ ለመረዳት አቅም የሚያጥረውም ሕዝብ አይደለም። ዛሬ ላይም እየሆነ ያለው ይሄው ነው። በሰላም ነገዎቹን የመፍጠር ቁርጠኝነት ነው።

ለዚህ ደግሞ ስለጦርነት እንደ አዲስ የሚሰብከው፤ የሚጮኽለት ኃይል አይፈልግም፤ ከትናንትም ከዛሬም ሕይወቱ በቂ ልምድ አለው። አሁን የሚፈልገው ሰላምና ልማትን የሚሰብከው ሐዋሪያ ነው። ወደ ነገ የተስፋው ዓለም የሚያሻግረውም መንገድ ይሄው ነው!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

# ‹‹ከ30 ዓመት በላይ ያለማነውን የአረንጓዴ ስፍራ ለወራሪዎች ተሰጥቶብናል››

**- አቤቱታ አቅራቢዎች**

ሙሉቀን ታደገ

**የዛሬው የ«ፍረዱኝ አምድ» ዝግጅታችን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ ገርጂ እየተባለ ወደሚጠራው አካባቢ ይወስደናል ።**

**«ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ስንገለገልበት የቆየነውን የአረንጓዴ ስፍራ (ግሪን ኤሪያ) በቦሌ ክፍለ ከተማ እና በወረዳ 14 የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተባባሪነት በሕገወጥ ወራሪዎች እንዲወሰድ ተደርጓል ። በወረዳው እና በክፍለ ከተማው የመሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተባባሪነት የተፈጸመብንን በደል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመልክቶ ይፍረደን» ሲሉ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የማዕድን ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነዋሪዎች ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል።**

**የዝግጅት ክፍሉም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ የደረሰበትን የክፍል አንድ ዝግጅቱን እንደሚከተለው ለንባብ አብቅቶታል።**

**ከአቤቱታ አቅራቢዎች አንደበት**

ለዝግጅት ክፍላችን አቤቱታውን ያቀረቡት የማኅበሩ ጸሐፊ አቶ ፈቃዱ በቀለ እና የማኅበሩ ሊቀመንበር አቶ ዘውዱ ንጉሴ ናቸው ።

እንደ አቤቱታ አቅራቢዎቹ ገለጻ ፤ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ ገርጂ አካባቢ እየኖሩ ነው። ይሄ ቦታ በ1983 ዓ.ም በማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ስም ተደራጅተው የተሰጣቸው ነው። ቦታው እስካሁንም ማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር እየተባለ ይጠራል።

በ1983 ዓ.ም መንግሥት ለማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር የመኖሪያ ቤት ቦታ ሲሰጥ ከመኖሪያ ቤቱ በተጨማሪ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሚገለገልበት የአረንጓዴ ስፍራ (ግሪን ኤርያ) ጨምሮ ነበር። ይህንን የአረንጓዴ ስፍራ (ግሪን ኤሪያ) የማኅበሩ አባላት ለ32 ዓመታት እያለሙ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ 2015 ዓ.ም የመስከረም ወር የመጀመሪያ ሳምንታት በነሩት ቀናት ላይ ለሰፋራቸው አዲስ የሆኑ እና ማንነታቸውን የማያውቋቸው የተለያዩ ሰዎች በአረንጓዴ ስፍራነት ወደ ተከለለው ቦታ አብዝተው መመላለስ ጀመሩ ። በዚህም ግራ የተጋቡት የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ለምን ወደ ቦታው እንደሚመላለሱ ይጠይቋቸዋል። ሰዎችም በቦታውን ሊገዙ መምጣታቸውን ያስረዳሉ።

ይህን ተከትሎ የማኅበር ነዋሪዎች «ሻጩ ማን ነው ?» ብለው ቦታውን ለመግዛት የመጡ ሰዎችን ይጠይቃሉ። ገዥዎችም አቶ ብርሃኑ ደገፋ የሚባሉ ሰው መሆናቸውን ተናግረው በአረንጓዴ ቦታነት በተከለለው ቦታ ላይ የተሠራውን ካርታም ያሳያሉ።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ነዋሪዎችም የአዩትን ማመን ከብዷቸው ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ ወረዳ 14 የከተማ ውበት እና የአረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት በመሄድ ስለተፈጠረው ነገር ያሳውቃሉ ። ጽሕፈት ቤቱም ስለጉዳዩ ምንም እንደማያውቅ ይነግራቸዋል።

በመሆኑም ጉዳዩን ለማሳወቅ ወደ ወረዳው አስተዳደር ያመራሉ። የወረዳው አስተዳደርም ስለጉዳዩ ምንም መረጃ የለኝም ብሎ ይመልሳል። ይህ በእንዲህ እያለ ጉዳዩ መፍትሔ ማግኘት ስላለበት አቤቱታ አቅራቢዎቹ ወደ ቦሌ ክፍለ ከተማ አመሩ።

የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደርና ልማት ጽሕፈት ቤት ፤ የመብት ፈጠራ እና ሌሎች የመሬትን ጉዳይ ለሚመለከቱ ቢሮዎችን በሙሉ ቅሬታቸውን በማመልከቻ አሳወቁ። ከላይ የተጠቀሱት የመሬትን ጉዳይ የሚመለከቱት ጽሕፈት ቤቶች የአቤቱታ አቅራቢዎች ማመልከቻዎች ከተመለከቱ በኋላ ጉዳዩን እንዲጣራ የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ለተባለው ክፍል መሩት ።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር አባላት ጉዳዩን እንዲጣራ ኃላፊነት የተሰጠው የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ የተባለው ክፍል የደረሰበት ውሳኔ ለማወቅ ወደ ቢሮው ያቀናሉ። ይሁን እንጂ የጠበቃቸው ውሳኔ አልነበረም። ስለአረንጓዴ ስፍራው (ግሪን ኤርያው) የማኅበሩ አባላት በእጃቸው ላይ ያሉ ማስረጃዎችን በሙሉ እንዲያመጡ ትዕዛዝ አንጂ። ይህን ተከትሎ የማዕድን ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነዋሪዎች አረንጓዴ ስፍራው (ግሪን ኤሪያው) የእነሱ ስለመሆኑ የሚያሳዩ ከ23 በላይ የሰነድ ማስረጃዎችን መሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ጽሕፈት ቤት አቀረቡ።

ሆኖም ግን ጉዳዩን እንዲያጣራ ኃላፊነት የተሰጠው መሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ጽሕፈት ቤት ሰነዶችን እንዲያቀርቡለት ከጠየቀ በኋላ የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ማኅበር ያቀረቡለትን ሰነዶች አልቀበልም አለ።

የመሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ክፍልም የማዕድን ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ተወካዮች የወሰዷቸውን ሰነዶች ተቀብሎን አልቀበልም በሚል ክርክር ይጀምራል ።

ተወካዮች እየተከራከሩ ሳለ በተመሳሳይ ሰዓት የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ማኅበር ተወካዮች ከሚኖሩበት ቦታ ወደ እጅ ስልካቸው የስልክ ጥሪ ደረሳቸው። የስልክ ጥሪውም የወረዳው መሬት ልማት ኃላፊ የቦታውን ካርታ ለተሰራለት ሰው አስረክባለሁ ብሎ መጥቶ ከነዋሪው ጋር ጭቅጭቅ መፈጠሩን የሚያሳውቅ ነበር ።

ወዲያውኑም ተወካዮች በእጃቸው የያዟቸውን ሰነዶች ለክፍለ ከተማው መሬት ማስተላለፍ ዘርፍ ጽሕፈት ቤት ሳይሰጡ ወደ ሰፈራቸው ይመለሳሉ። የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ኃላፊ ለአረንጓዴ ስፍራ የታጠረውን ቦታ ለወራሪዎች አስረክባለሁ ብሎ ከሰፈር ሰዎች ጋር ሲጨቃጨቁ ይደርሳሉ።

ይህን ተከትሎ «በምን አግባብ ነው ቦታውን የምታስረክቡት? ከዚህ በፊት እናንተ ቢሮ መጥተን ‹ ስለጉዳዩ ምንም መረጃ የለንም ስትሉን አልነበረም ወይ? እንዴት ጉዳዩን ለክፍለ ከተማው ለማሳወቅ በሄድንበት ያለማኅበሩ አባላት እውቅና መሬቱን ለወራሪዎች ለማስረከብ መጣችሁ? »ሲሉ የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ኃላፊ ይጠይቃሉ ።

አከታትለውም በቦታው ስለተፈጠረው ነገር የአካባቢው ማኅበረሰብ ለክፍለ ከተማው ጥያቄ አቅርቦ መልስ በሚጠባበቅበት በዚህ ሰዓት ወረዳው ለምን መሬቱን ለወራሪዎች እናስረክባለን ይላል? ለማንስ ነው የምታስረክቡት? በማለት የወረዳውን መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ይጠይቃሉ። የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊም ቦታውን የሚያስረክበውም ቦታውን ተሰጠው ለተባለው ሰው ሳይሆን በውክልና ለመጣ ሰው መሆኑን ይነግራቸዋል።


ይህን ተከትሎ የማዕድን ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነዋሪዎችም በአዲሱ መመሪያ መሠረት የመሬት ጉዳይ በውክልና እንደማይስተናገድ ያዝዛል። ስለዚህ መመሪያ ጥሳችሁ ስለምን በወኪል አማካኝነት መሬቱን ታስረክባላችሁ? ቦታው ተሰጥቶታል የምትሉት ሰው 400 ካሬ ሜትር ነው ። የማህበሩ ግሪን ኤሪያ ስፋት ደግሞ 700 ካሬ ሜትር ነው። እንዴት አድርጋችሁ ነው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ መሬቱን ልትሰጡ እና ልትሸነሽኑት የምትችሉት? መሬቱን ማስረከብ ያለበት ክፍለ ከተማው እንጂ ወረዳው ነው ወይ? ጉዳዩ መስተናገድ አለበት ሕግ እና ሥርዓቱን ጠብቆ እንጂ እንዴት ሕግና ሥርዓትን ባልተከተለ አግባብ መሬቱን ልትወስዱ ትመጣላችሁ? በማለት ጥያቄ ያነሳሉ።

መንግሥት ቦታውን ለልማት ከፈለገው እና ሕጋዊ መንገድን ተከትሎ ከመጣ አይደለም ግሪን ኤሪያውን መኖሪያ ቤታቸውም ቢሆን አፍርሶ መውሰድ እንደሚችል፤ ነገር ግን ሕግ እና ሥርዓትን ባልተከተለ አግባብ ሲመጣ ግን የሃገርን ሕልውና የሚጻረር በመሆኑ የትኛውንም አይነት ውሳኔ እንደማይቀበሉ ለወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ያስረዳሉ።

ይህ በእንዲህ እያለ በነዋሪዎቹ እና በወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ኃላፊ መካከል አለመግባባቱ በጣም ይሰፋና ወደ ጭቅጭቅ ያመራሉ። የተፈጠረውን ጭቅጭቅ ለማብረድም ፖሊስ ጣልቃ ይገባል።

ፖሊስ የተፈጠረውን ችግር ለማብረድ በገባበት ወቅት አቤቱታ አቅራቢዎቹ መሬቱን አዲስ ለተመራው ሰው እንድታስረክቡ የታዘዛበት ደብዳቤ አላችሁ ወይ ? አሳዩን በማለት ጥያቄ ያነሳሉ።

የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት



በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር ጽ/ቤት — Bole Sub City Woreda 14 Administration office

አባሪ 3

ቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/14/1/ 466 /2011

ቀን 27/03/2011

ለ..........................ሸማች ማህበር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- አስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃ እንድትወስዱ ስለማሳሰብ ፤

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት በቀን 21/3/2011 ዓ.ም በቁጥር ቦ/ክ/ከ/መ/ባ/ማ/1572/11 በተፃፈ ደብዳቤ የተወረሩ አረንጓዴ ቦታዎችን በተመለከተ በሚል ርዕስ ሥር በወረዳችን የሚገኙትን አረንጓዴ ቦታዎችን ያሉበትን ሁኔታ በዝርዝር በማየት ህገ ወጥ የሆኑትን በመለየት ህጋዊ እርምጃ ወስደን እንድናሳውቅ ተጠይቀናል ፡፡ በመሆኑም በ..........ሸማች ማህበር ሥር እየተዳደረ የሚገኘው አረንጓዴ ቦታ ከታለመለት አግባብ ውጭ ለዕድር ቤት ፡ለመኪና ማሳደሪያ ፡ ለሸማች ማህበር ፡ በግለሰቦች የተወረረ በመሆኑና በተደጋጋሚ ለታለመለት አግባብ ብቻ እንዲውል የወረዳችን ውበትና መናፈሻ ጽ/ቤት በቃልና በፁሁፍ ቢያሳውቅም እስካሁን ምንም አይነት ለውጥ ማምጣት አልታቻለም ፡፡ ስለዚህ የወረዳው አስተዳደር ከክ/ከተማው በተሠጠው መመሪያ መሠረት አረንጓዴ ቦታዎችን ለታለመላቸው አላማ ብቻ እንዲውሉ ለማድረግ ሲባል በ5 ቀናት ውስጥ በአረንጓዴ ቦታዎች የተከማቹ ተሸከርካሪዎች እንዲወጡ በወረራ የተገነቡ ቤቶች እንዲፈርሱ እያሳሰብን ይህን በተቀመጠው ቀን በማይፈፅሙ ማህበራትና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ የሆነ እርምጃ ከማሸግ ጀምሮ እንደሚወስድ እናሳስባለን ፡፡


ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ ፤

በወረዳ 14 አስተዳደር

ለጥና ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ ፤



የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን — Addis Ababa Water & Sewerage Authority

አባሪ 8

8783339

97049 — April 2005 — 1997

Misrak — E1-309 — 1358

5-17-25-97049-1

2821185 — 0.5

MAADNNA ENERGY YEMENORIA BET — coll c. Gerji — /1 - 5

ወረዳ 17 — ቀበሌ 25 — የቤት ቁ. 0000

የውል ቁ. 171978 — Domestic

ፍጆታ — 1 — 1.45 — 1.45

1.35

0.07

ጠቅላላ Total ********2.87

Decrease

ከሰኔ 1996 ዓ.ም ጀምሮ ለጽዳትና ውበት አገልግሎት በውሃ ፍጆታ ሂሳብዎ ላይ 5% ክፍያ የተጨመረ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

Please do not accept forged (deleted/erased) bill

# ፍረዱኝ

ቤት ቦታውን አስረክባለሁ የሚለው የቤት ኪራይ እና ቦታ ግብር አወሳሰን የሚል ወረቀት ይዞ መሆኑን ይነግራቸዋል። በዚህ አይነት በነዋሪዎች እና መሬቱን ለማስረከብ ከመጣው ሰው ጋር ሌላ አምባ ጓሮ ተፈጠረ። ፖሊስም ጣልቃ ገብቶ የወረዳው መሬት ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊውን ቦታውን አስረክብ ስለመባሉ የሚያሳይ ደብዳቤ እንዲያመጣ ጠየቀ። ከሁለት ቀን በኋላም ከክፍለ ከተማ መሬት ልማት ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ እንዲያመጣ ነገራቸው ።

ከሁለት ቀን በኋላ ደብዳቤ አመጣለሁ ብሎ የነበረው የወረዳው መሬት ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊም በተባለው ቀን ደብዳቤ ሳያመጣ ቀረ። ይልቁንም «የቦታው (ግሪን ኤሪያው) ባለቤት ነን የምትሉ ከሆነ በቦታው ላይ ያሏችሁን ማስረጃዎች ይዛችሁ በሁለት ቀን ወረዳው ጽሕፈት ቤት እንድትመጡ » የሚል ከግሪን ኤሪያው አጥር በር ላይ ማሳሰቢያ ለጥፎ ሄደ ። ማሳሰቢያውን ለነዋሪዎቹ በቀጥታ የተሰጠ አልነበረም ።

ይህን ተከትሎ የአካባቢው ነዋሪዎችም በአረንጓዴ ስፍራው ላይ መብራት እና ውሃ ያስገቡበትን፣ አረንጓዴ ስፍራውን ( ግሪን ኤሪያውን) ለማልማት እንቅስቃሴ ያደረጉባቸውን እና በጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ሃሳብ አመንጭነት አረንጓዴ አሻራ በሃገር ደረጃ መጀመር ጋር ተያይዞ ምን ያህሉ አረንጓዴ ስፍራውን (ግሪን ኤሪያውን) ለአረንጓዴ ልማት መዋል አለበት፣ ምን ያህሉ ደግሞ ለሌሎች ተግባራት መዋል አለበት የሚል ዲዛይን በማሠራት የዲዛይኑን ኮፒ እና ሌሎች አሉ የሚባሉትን ሰነዶች ለወረዳው ያቀርባሉ።

እንደአቤቱታ አቅራቢዎቹ ገለጻ፤በአጋጣሚ የሚኖሩበት አካባቢ ዙሪያውን ካባ እየተባለ የሚጠራው ድንጋይ እየወጣ የሚሸጥበት ነው። የመኖሪያ ሰፈሩ በካባ አውጭዎች እንደ ደሴት ሆኗል።

የካባ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የመኖሪያ ሰፈሩ ከስድስት በላይ መውጫ እና መግቢያ ነበሩት ። አሁን ላይ የካባ ድንጋይ በሚያወጡ ሰዎች ምክንያት መውጫ መግቢያው ተበልቶ አሁን ብቸኛ መውጫ መግቢያ የቀረው የግሪን ኤሪያው የሚገኝበት ብቻ ነው ። አሁን ይህ ግሪን ኤሪያ ቢወሰድ የሰፈሩ ሰዎች በሙሉ መውጫ አይኖራቸውም ።


በሰፈሩ ደስታ እና ኃዘን ሲያጋጥምም ድንኳን ሲተከል እንኳን ለመግባት እና ለመውጣት የሚገጥማቸው ፈተና ከባድ መሆኑን ያስረዳሉ። ስለሆነም የግሪን ኤሪያው ቦታ የሰፈሩ ሰዎች መተንፈሻ መሆኗን አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

**ከአቤቱታ አቅራቢዎች የተገኙ ሰነዶች ምን ይላሉ?**

**ሰነድ አንድ፡-** የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት የሥራ ማኅበር በቀን 6/7/1996 ዓ.ም በቁጥር ማኤቁ4ሥማ/96 ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የምስራቅ ዲስትሪክት ቁጥር አራት ጽሕፈት ቤት በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት የሥራ ማኅበር በኅብረት የሚጠቀሙበትን መናፈሻ ቦታ (ግሪን ኤሪያ) አገልግሎት ለማሳደግ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ ፤ ነገር ግን ሰፈሩ አዲስ በመሆኑ የተነሳ የውስጥ ለውስጥ መብራት እና ሌሎች አገልግሎቶች ስለሌለው በተለያዩ ጊዜያት ችግሮች መከሰታቸውን ፤ ስለሆነም በሰፈሩ ያለውን የጸጥታ ችግር ለማስወገድ ማኅበሩ በጋራ በሚጠቀምበት መናፈሻ ቦታ (ግሪን ኤርያ) ላይ የኤሌክትሪክ ቆጣሪ እንዲገባላቸው እና በቂ የመንገድ መብራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይጠይቃሉ።

ማኅበሩ ያነሳውን ጥያቄ ተከትሎ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በውል ቁጥር 483447 እና በደንበኛ ስም ማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ነዋሪዎች ስም 220 ቮልት ቆጣሪ በ22/07/1996 ዓ.ም እንደተሰጣቸው ሰነዶች ያመለክታሉ ።

**ሰነድ ሁለት፡-** በቀን 5/13/1995 ዓ.ም ቁጥር ማኢቁ4ቤሥማ13/95 በማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ማኅበር ስም በተጻፈ ደብዳቤ የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን


የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን
አባሪ 7
ETHIOPIAN ELECTRIC POWER CORPORATION
ስለ ኤሌክትሪክ ማደል የተደረገ ውል
CONTRACT FOR SUPPLY OF ELECTRICITY
የውል ቁጥር Contract No 483447
የደንበኛው ስም Customer's name
አድራሻ Address
የሚፈለገው ኤሌክትሪክ የሚውልበት አገልግሎት Purpose for which electricity is to be supplied Residential Purpose
ደንበኛው በኤሌክትሪክ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ዝርዝር
DETAILS OF EQUIPMENT INSTALLED

| መሣሪያ Apparatus | ብዛት No. of Points | የሽማ ብዛት Total Wattage | መሣሪያ Apparatus | ብዛት No of Points | የሽማ ብዛት Total W... |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| መብራት Lighting | | | ሞተሮች Motors | | |
| መሰኪያ Socket outlet | | | ልዩ ልዩ መሣሪያዎች Miscellaneous | | |
| የውሃ ማሞቂያና ማብሰያ Water Heating and Cooking | | | | | |

የተፈቀደው ጉልበት Power Approved
ኪዋ KW
ቮልት Volt 220V
የሚፈጸመው ታሪፍ Applicable Tariff 10
ቀን Date 22/07/96
ማስያዣ የኢ.ት. ብር Deposit Eth.
የኤሌክትሪክ መቀጠያ ዋጋ የኢ.ት.ብር Connection fee Eth. 10000
ድምር የኢ.ት. ብር Total Eth. 8304.02
የደረሰኝ ቁ. Receipt No 2041924
ቀን Date 28/07/96
የደንበኛው ፊርማ Customer's Sign
WONDALE MUNYE
የባለሥልጣኑ ፊርማ For the Authority

የምሥራቅ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ለግሪን ኤሪያው ውሃ እንዲገባላቸው መጠየቃቸውን እና በጥያቄአቸውም መሠረትም የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ምሥራቅ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በማእድን እና ኢነርጂ የመኖሪያ ቤት ስም 2821185 ቁጥር የተመዘገበ የውሃ ቆጣሪ በሚያዚያ ወር 1997 ዓ.ም እንደሰጣቸው በሰነዶቹ ላይ ያሳያሉ።

**ሰነድ ሶስት፡-** በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በቀን 27/03/2011 ዓ.ም በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/14/ 1/466/2011 ለማዕድን እና ኢነርጅ ቁጥር አራት ማኅበር አስቸኳይ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የሚያሳውቅ ደብዳቤ ተጽፏል።

ለዚህ ደብዳቤም መነሻ ምክንያትም የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት በቀን 21/3/2011 ዓ.ም በቁጥር ቦ/ክ/ከ/በ/ባ/1572/11 ለወረዳ 14 በጻፈው ደብዳቤ በሕገወጥ መልኩ የተወረሩ የአረንጓዴ ቦታዎችን ለታለመላቸው አገልግሎት እንዲመለሱ ማስጠንቀቁን ተከትሎ ነበር።

ይህን ደብዳቤ ተከትሎ በወረዳ 14 ከሚገኙ የአረንጓዴ ቦታዎችን መካከል በማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ስር እየተዳደረ የሚገኘው የአረንጓዴ ቦታ መሆኑን ጠቅሶ ይህ ቦታ ከታለመለት አግባብ ውጭ ለእድር ቤት ፣ ለመኪና ማሳደሪያ፣ ለሸማች ማኅበር እንዲሁም፣ ለሌሎች ተግባራት እየዋለ በመሆኑ የግሪን ኤሪያው ለታለመለት ሥራ የማይውል ከሆነ እርምጃ እንደሚወሰድ የሚያስጠነቅቅ ነው።

**ሰነድ አራት፡-** በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/14/0.3/795/2014 በቀን 02/10/2014 ለማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት የማኅበር በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው በወረዳ 14 በማዕድን ቁጥር አራት ማኅበር አረንጓዴ ቦታ ውስጥ ያሉ መኪኖች ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆናቸው ይጠቅሳል ። በመሆኑም በማኅበሩ ግቢ ውስጥ ችግኝ ለመትከል ስለተፈለገ እና መኪኖቹም የማኅበሩን ውበት ስላበላሹ ይህ ደብዳቤ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ እስከ 7/10/14 ዓ.ም ድረስ በአስቸኳይ እንድታነሱ እያስጠነቀቀ የማያነሱ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን የሚጠቁም ነው ።

**ሰነድ አምስት፡-** በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/14/0.3/470/2013 በቀን 27 02/2013 ዓ.ም ለማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው የወረዳው አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት በማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት በሚገኘው አረንጓዴ ስፍራ የተተከሉ ችግኞችን እንዲንከባከቡ የሚጠይቅ ነው ።

**የወረዳው መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ምላሽ**

ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከሆኑት አቶ ፈይሳ ሙሉጌታ ጋር ተገናኝተን በማዕድንና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ስር የሚገኘውን የአረንጓዴ ስፍራ ለሦስት አስርተ ዓመታት በአረንጓዴ ስፍራነት ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን እና ቦታው የእነሱ ስለመሆኑ የማኅበሩ አባላት ይናገራሉ ። ስለዚህ ምን ይላሉ ? የሚል ጥያቄ አንስተንላቸው ነበር ።

እሳቸውም‹‹ማኅበሩ ቦታውን ለ30 ወይም 40 ዓመታት በአረንጓዴ ስፍራነት ሊጠቀሙት ይችላሉ። ነገር ግን በመመሪያው መሠረት ለበርካታ ዓመታት የአረንጓዴ ስፍራውን ተጠቀሙ ማለት በቦታው ላይ ባለመብት ይሆናሉ ማለት አይደለም›› ሲሉ ገልጸውልናል።

የክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር ከዚህ ቦታ ጋር ተያይዞ መረጃዎችን ሲያሰባስብ መቆየቱን የሚናገሩት ኃላፊው፤ የማዕድንና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ይህንን ቦታ እንዲጠቀም የፈቀደ ማንም መንግሥታዊ ተቋም አለመኖሩን ይገልጻሉ። መንግሥትን ሳይጠይቁ ውሃ እና መብራት ስላስገቡም ቦታው የማኅበሩ ነው ማለት እንደማይቻል ያስረዳሉ። ቦታው በጂአይ ኤስ እንደማይታይም አመላክተዋል። በጂአይ ኤስ የማይታይ ቦታም ሕጋዊነት እንደሌለው ይናገራሉ ።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ማኅበሩ ከከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት ጋር ተነጋግረው ለበርካታ ዓመታት በአረንጓዴ ስፍራ ቢያለሙትም ጂአይ ኤስ እስከሌለው ድረስ ሕጋዊ አይደለም ብለውኛል ። ይህን የሚል መመሪያ አለ ወይ? መመሪያውን ቁጥር ጠቅሰው ይንገሩኝ ። ጥያቄውን ተከትሎ አቶ ፈይሳ የትኛው መመሪያው እንደሆነ እርግጠኛ እንዳልሆኑ ነገር ግን በከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት የሚተዳደር ካርታ እስከሌላቸው ድረስ ሕጋዊ አለመሆናቸውን ተናግረዋል።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ከከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት ጋር ውዝግብ ያስነሳውን ቦታ እንዴት በጋራ ማልማት እንዳለባቸው ለበርካታ ዓመታት ሲጻጻፉ እና ሲያለሙ እንደነበር ይታወቃል። ሕገ ወጥ ከሆኑ የእናንተ መሥሪያ ቤት እስከዛሬ ለምን አላስቆመም ? በዚህ ዓመት(በ2015ዓ.ም) ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው መሬቱ በአረንጓዴ ስፍራ አልተካተተም ልትሉ የቻላችሁት? ሲል የዝግጅት ክፍል የጠየቃቸው ኃላፊው፤ ‹‹የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሕጋዊ እንዳልሆነ ነግሯቸው ነበር›› ሲሉ መለሱ። አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም የጠየቃችሁበትን ደብዳቤ ልታሳዩን ትችላለችሁ ? ሲል ኃላፊውን ጠየቀ ። ኃላፊውም ከዚህ በፊት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዳልሰጡ ፤ ነገር ግን በቃል እንደነገሯቸው መለሱ። በቃል የሚሰጥ ትዕዛዝ ከሕግም ሆነ ከመመሪያ አኳያ ተቀባይነት የለውም ። ስለዚህ በደብዳቤ ያስጠነቀቃችሁበት ካለ ልታሳዩን ትችላችሁ? ሲል ደግሞ ጠየቀ። ነገር ግን ይህ ነው የሚባል ምላሽ መስጠት ሳይችሉ ቀሩ ።

የማዕድን እና ኢነርጂ ቁጥር አራት ማኅበር ከወረዳው እና ከክፍለ ከተማው የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር ሲጻጻፉ ቆይተዋል። ማኅበሩ ሕገ ወጥ ከሆነ ማኅበሩ ከወረዳው እና ከክፍለ ከተማው የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማትን ቢሮ ጋር ሲጻጻፍ የክፍለ ከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ማኅበሩ የሚያለማው ግሪን ኤሪያ ሕገወጥ ስለመሆኑ በደብዳቤ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አላችሁ? ሲል ጠይቆ ነበር ፡። ሆኖም ኃላፊው ‹‹የለንም። ስለዚህ የማውቀው ነገር የለም›› የሚል መልስ ሰጥተውናል። ይህ የክፍለ ከተማው መሬት ልማት እና አስተዳደር ማስጠንቀቂያ ካልሰጠ ዛሬ ላይ ማለትም በ2015 ዓ.ም ሲለማ የኖረን ግሪን ኤሪያ ሕጋዊ አይደለም ልትሉ እንዴት ቻላችሁ? ሕገ ወጥ ከሆነ ስለምን መብራት እና ውሃ ሲገባ ዝም አላችሁ? ተብለው የተጠየቁት ኃላፊው የክፍለ ከተማው መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አስቁመዋል የሚል ምላሽ ሰጡ ። ካስቆመ ያስቆመበት ደብዳቤ ያሳዩን ስንል ጠየቅን ። ሆኖም ኃላፊው ደብዳቤ አለመኖሩን ነው ያረጋገጡልን።

**ከአዘጋጁ፤**

ውድ አንባቢያን በማዕድንና ኢነርጂ ቁጥር አራት የመኖሪያ ቤት ማኅበር እና በወረዳ 14 እንዲሁም በቦሌ ክፍለ ከተማ መካከል የተከናወኑትን የደብዳቤ ልውውጦች በመመልከት ለአለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት የአረንጓዴ ስፋራው (ግሪን ኤሪያ) የማን ነበር የሚለውን፤ ከሕግና መመሪያ አንጻር ኃላፊዎች ሥራዎቻቸውን በምን መልኩ እየተወጡ ነው የሚለውን ለአንባብያን እንተወዋለን።

በቀጣይ ለሚኖረን ዘገባ በወረዳው እና በክፍለ ከተማው የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ግለሰቦችን በማነጋገርና ሰነዶችን በማካተት ቀጣዩን ክፍል ሁለት የምናቀርብ ይሆናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ዕርቀ ሰላም ደም ያድርቅ

(ክፍል አንድ)

**ትዝብተ ሰብእ፤**

በሰዋዊ የባህርያችን ትዝብት እንንደርደር። መራር ነገር ወደ ሆድ፣ ወደ ልብም ሆነ ወደ ስሜት ዘልቆ ለመግባት በእጅጉ ይገዳደራል። የልብንና የስሜትን ተግዳሮት ጉዳይ ወደ ኋላ ግድም ስለምንመለስበት ለጊዜው ወደ ሆድ ውስጥ የሚገባ መራራ ነገር ምላሳችንን ገና መንካት ሲጀምር የሚገጥመውን ፈተና በተመለከተ አንድ ግልጽ ማሳያ አስታውሰን ወደ ሌሎቹ ጉዳዮች እናመራለን።

የሰው ልጅ ወደ ሆድ ውስጥ የሚገባን መራር ነገር ለማጣፈጥ በፈጠረው ዘዴ እየተጠቀመ “መራራ ጠላቱን” ማሸነፍ ከጀመረ ዘመናት አስቆጥሯል። እንደ መተሬ ወይንም እንቆቆ የመረረ ባህላዊ መድኃኒት በሌሎች ሀገራት ባህል ውስጥ ይኑር አይኑር እርግጡን ለማወቅ ጥልቅ ምርምር ይጠይቃል። አይኖርም ለማለቱ ድፍረት ባይኖረንም የሀገራችንን ያህል በቁም እንደሚያንዘፈዝፉት እንቆቆና መተሬ ብርታት ይኑራቸው አይኑራቸው ለመገመት ይከብዳል።

ብልሁ የሀገሬ ሰው መተሬን የመሰለ መራር የባህል መድኃኒት “እየተቌለ” ወደ ሆድ እንዲዘልቅ የፈጠረው ጥበብ አጃኢብ ያሰኛል። እንኳን ሲቀምሱት ቀርቶ ስሙን ሲጠሩት ምሬቱ በስሜት የሚያንገሸግሸው መተሬ የሚወሰደው በሙዝ ወይንም ቤት ባፈራው ፈጠራ (ብዙ ጊዜ ገንፎ) እየተጠቀለለ ነው። ከዚያማ ምን ይጠየቃል ለቅጽበት ምላስን አጣፍቶ ወደ ሆድ የወረደው መተሬ እንክብል ተልዕኮውን አጠናቆ ከጥገኛ ትላትል የሚፈውሰው በሚያስደንቅ ፍጥነት ነው።

እንደሚመስለን ይህንን ባህላዊ ዘዴ መነሻ ያደረጉ የዘመናዊ መድኃኒት አምራች ኩባንያዎች መራራ ኪኒኒዎች (ታብሌቶች) ምሬታቸው ሳይታወቅ እንዲዋጡ ለማድረግ ከምላስ እስኪወርዱ ድረስ ስኳር በመቀባት (Sugar Coated Tablets) ባህላዊውን ዘዴ በዘመናዊ ጥበብ ሳይተኩት አልቀረም።

**“ሰማይ ተቀደደ ቢሉት፤ ሽማግሌ ይሰፋዋል አሉት”፤**

ይህ ባህላዊና ዘመናዊ የምሬት ማለሳለሻና ማጣፈጫ ዘዴ እንደ መንደርደሪያ ሊጠቀስ የተፈለገበት ዋና ምክንያት ለሰላምና ይቅርታ ጥሩ የማሳያ አብነት ስለመሰለን ነው። የሰው ልጅ ለተለያዩ የፍቅር መገለጫዎች እጁን የሚሰጠው ቢግደረደርም ሳይዘገይ ነው። በውስጡ የተዳፈነውን ድፍረት፣ ወኔ፣ ጀግንነትም ሆነ ሌሎች አወንታዊ ስሜቶች ለክፉም ይሁን ለደግ ለመግለጽ ስሜቱ ቅርብ ነው። ግፋ ቢል መቆስቆሻው ፉከራ፣ ቀረርቶ፣ ወይንም “ጨክን” ይሉት አይነት ስሜት ማነሻሻዎች በቂና ከበቂ በላይ ናቸው።

ለይቅርታና ለሰላምስ? አንባቢው መልስ ለመስጠት የሚቸገር አይመስለንም። ሰላምና ዕርቅን ለማስፈን የሰው ልብ ምን ያህል በምሬት እንደሚሞላ በብዙ ማሳያዎች ማመላከት ይቻላል። ሰላምን አሜን ብሎ አክብሮ ዝቅ ለማለት ጭንቅ ጥብብ ያደርጋል፣ ያስምጣል፣ ስሜት በውስጥ ማንነታችን ይፋጫል፣ ይጋጫል፣ ይታወካል። በተለይማ ይቅር ተብሎ ሰላም እስኪወርድ ድረስ ያለው የምጥ ጣር ከወላድ እናት ምጥ ቢስተካከል እንጂ የሚያንስ አይሆንም። እኮ ስለምን ይሆን የሰው ልጅ “አጥፍቻለሁ” እና “ለሰላም እጆቼን ዘርግቼ ይቅርታውን ተቀብያለሁ!” ለማለት የሚቸገረው?

ለሰላምና ለዕርቅ የሚደረጉ የሽምግልና ድርድሮችና ውጣ ውረዶች በመተሬ መጠቅለያ ሙዝ ወይንም በስኳር ቅብ ኪኒኒዎች የሚመሰሉትም ስለዚሁ ነው። ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ (ፕሪቶሪያ) የተደረሰበት ስምምነት ውጤቱ ለአሥር ቀናት ሲዘገይ በጉጉትና በልብ መንጠልጠል እንዲጠበቅ ምክንያት የሆነው በተለይም በሕወሓት በኩል ይኼው ሰዋዊ ባህርይ ትንቅንቅ ስለገጠመው ይመስለናል።

ኢትዮጵያ በዚህ ንግግር ገና ከጅማሬው ልቧን ለሰላም ክፍት አድርጋ በመዘጋጀት “መቶ በመቶ” ለማሸነፍ የበቃችው ከላይ የተጠቀሰው መሰል ሕዝባዊ የዕለት ተዕለት ባህሏና የከበረው ታሪኳ ብዙ ስላስተማራት እንደሆነ ለማመን አይከብድም።

> **ሰላምና ዕርቅን ለማስፈን የሰው ልብ ምን ያህል በምሬት እንደሚሞላ በብዙ ማሳያዎች ማመላከት ይቻላል። ሰላምን አሜን ብሎ አክብሮ ዝቅ ለማለት ጭንቅ ጥብብ ያደርጋል፣ ያስምጣል፣ ስሜት በውስጥ ማንነታችን ይፋጫል፣ ይጋጫል፣ ይታወካል። በተለይማ ይቅር ተብሎ ሰላም እስኪወርድ ድረስ ያለው የምጥ ጣር ከወላድ እናት ምጥ ቢስተካከል እንጂ የሚያንስ አይሆንም። እኮ ስለምን ይሆን የሰው ልጅ “አጥፍቻለሁ” እና “ለሰላም እጆቼን ዘርግቼ ይቅርታውን ተቀብያለሁ!” ለማለት የሚቸገረው?**

በሁለቱ አካላት መካከል የተደረሰበት የሰላም ንግግር እንዲቋጭ የኢትዮጵያ መንግሥት ልቡን ያሰፋው በሀገሪቱ ላይ የተፈጸመው ግፍ ቀላል ስለነበር፣ የፈሰሰው የንጹሐን ደም ስለተዘነጋ፣ የተፈናቀሉና ሥነ ልቦናዊ ቀውስ የደረሰባቸው ዜጎች እምባ ስለታበሰ ወይንም የወደሙት ንብረቶችና ሀብቶች በቀላሉ ስለታዩ አይደለም። በፍጹም። እነዚህ በደሎች ለዛሬውም ሆነ ለመጻኢው ትውልድ ጠባሳቸው በቀላሉ ይሽራል ተብሎ ስለታመነበትም አይደለም።

ይልቁንስ የመሪዎቻችን የማስተዋል ጥበብ፣ የአማካሪ ወዳጆቻችን የከበረ ቃልና የመላው ሕዝብ ኢትዮጵያ ጸሎት፣ መሻትና ጉጉት ዋናው መግፍኤ ምክንያት ስለሆነ ነው። የፈሰሰን ደም የሚያደርቀው፣ የቆሰለን ስሜት የሚፈውሰው በጦርነት በማሸነፍ በሚገኝ ድል ብቻ ሳይሆን ዋናው መደላድል “እርቀ ሰላም” በማዕከላዊነት ሲሰፍን ብቻ ነው።

በአንጻሩ የወዲያኛው ቡድን ቤተኞች የሆኑ “የዲያስፖራ ምን ግዴዎች” የሰላም ንግግሩ “በሰላም” መቋጨቱ እያንገበገባቸው የሚኖርባቸውን ባዕዳን ሀገራት የሚያምሱት፣ አደባባዮችን የሚያውኩት፤ አውራ ጎዳናዎችን የሚዘጉትና የየሀገሩ የመንግሥታዊ ተቋማት ባለስልጣናት በሰላም ተግባራቸውን እንዳይከውኑ በጩረባ ጩኸት እያወኩ ሰላም የሚነሱት በርግጠኝነት “ሕዝባችን” እያሉ በአንደበታቸው ብቻ ለሚያንቆለጳጵሱት የትግራይ ሕዝብ ተጨንቀው ሳይሆን “የሰላም ንግግሩ መቋጨት” የእነርሱን እኩይ ዓላማ ተርትሮ እርቃናቸውን እንዳያጋልጣቸው ፈርተው ጭምር ነው። በጦርነቱ የሚፈሰው የንጹሐን ደምና የሚወድመው የሀገርና የዜጎች ሀብት ግድ ያልሰጣቸው “ከልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ እንደሚውሉት የኮምፒውተር ጌም” የሕዝባችን ሞትና መፈናቀል ስለቀለለባቸው ጭምር ነው።

በአንድ ሀገር ዕርቀ ሰላም የሚሰፍነው አስተዳዳሪው መንግሥት በሚወስዳቸው ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ የልብ ስፋት ብቻም አይደለም። ዜጎችም ልባቸው ሊሰፋ፣ መንፈሳቸው ተረጋግቶ በምሕረትና በይቅርታ ዝግጁ ሲሆኑም ነው። በተለይም ለመቶ ፐርሰንት ጥቂት ፊሪ የሆነው ሕዝቧ በአንድም ሆነ በሌላ የእምነትና የሃይማኖት ቤተሰብ አባል ነው በሚባልበት ሀገርና በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት “ይቅርታና ሰላም” እንደ ክረምት ዝናብ በሚዥጎደጎድባት ኢትዮጵያ ምሬትን ሳይሆን ምሕረትን ማስቀደም ችግር ባልሆነ ነበር።

በደልን ይቅር መባባልና ከሰላም ጋር መስማማት ለውስጥ ስሜት ፈውስን፣ ለሀገር በረከትና እረፍትን፣ በፈጣሪም ዘንድ በእጅጉ የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይጠፋዋል ተብሎ አይገመትም። ችግሩ “ካፈርኩ አይመልሰኝ” እብሪትና የልብ ድንዳኔ እንደ ጭንጫ ጠንክሮ እልሸኛ ስለሚያደርግ ብቻ ነው። ከወዲያኛው ወገን የሚደመጠው “ዲያስፖራዊ የቁራ ጩኸት” ምክንያቱ ሌላ ሳይሆን ይሄው አፍቅሮተ ራስና ከእኛ ወዲያ ለአሳር ልክፍት ነው።

ይህ ጸሐፊ ስለ እርቀ ሰላም ሲያስብ ሁሌም ፈጥኖ ወደ አዕምሮው የሚመጣና በብዙ አጋጣሚዎች የሚጠቅሰው አንድ ታሪክ ይታወሰዋል። ታሪኩ ልቦለድ ሳይሆን በደቡብ የሀገራችን ክፍል በሀዲያ ዞን፣ በሶሮ ወረዳ በአምሸራ ቀበሌ የተፈጸመ ነው። ስማቸው የሚጠቀሰው ባለታሪኮችም እውነተኞቹ የድርጊቱ ፈጻሚዎች መሆናቸውን ማረጋገጫ እንሰጣለን። ወደ ትረካው እንዝለቅ።

አቶ ለቴቦ አርበጮ የሚባሉ አንድ አባት ዕድሜዋ ሰባት ዓመት የሆናት መካሜ የምትባል ሴት ልጅ ነበራቸው። በሆነ አጋጣሚ በተፈጠረ ሁኔታ አቶ ለቴቦ ከሚጎራበታቸው አንድ ቤተሰብ ጋር የከረረ ፀብ ውስጥ ገብተው ነበር። ይህንን ፀባቸውን በእርቀ ሰላም ለመፍታት የሚያስችል ሙከራም በሁለቱ ጎረቤታማቾች መካከል ሳይፈጸም ቀናት ነጉደዋል። ሁለቱም ቤተሰቦች በየቤታቸው አንዱ የሌላውን በደል እየተረከ ሲያወራ ውሎ የሚያድረውም የየቤቱ ሕጻናትና ወጣት ልጆቻቸው ባሉበት ስብስብ መካከል ነበር። ይህ በቁጭትና በእልህ ሲወራ የኖረው ቂምና ቁርሾ ከአዋቂዎቹ ይልቅ በታዳጊ ልጆቹ ዘንድ እጅግ ምሬትን መፍጠሩን ታላላቆቹ ልብ ሊሉ አልቻሉም።

አንድ ዕለት ከጠበኞቹ ቤተሰቦች መካከል የአንደኛቸው ታዳጊ የአሥራ ሁለት ዓመቱ ማቴዎስ ቤተሰቦቹ ሲያወሩ በሰማው ድርጊት በከፍተኛ ሁኔታ ስላቄመ ሌላኛውን ቤተሰብ ለመበቀል ልቡ ለክፋት ድርጊት መነሳሳት ጀመረ። ስለሆነም የአቶ ለቴቦን ቤተሰብ ለመበቀል በማሰብ ትኩረቱን በሰባት ዓመቷ መካሜ ላይ ማድረግን ተያያዘው። እንዴት ይህቺን ታዳጊ ገድሎ የቤተሰቡን ቂም እንደሚፈውስም ማሰላሰል ጀመረ። አሰላስሎ ብቻም አልተወም እንዴትና መቼ ዕቅዱን ለመተግበር እንደሚችልም ራሱን ዝግጁ አደረገ።

በአንድ ክፉ ዕለት መካሜ ከብቶች እየነዳች ወደ ወንዝ ስትወርድ ማቴዎስ ከበስተኋላዋ እየተከተላት እንደነበር አልጠረጠረችም። ማቴዎስ ድንገት እመር ብሎ እጅና እግሮቿን ጠፍሮ ካሰረ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ ገደላት። አስከሬኗ እንዳይገኝም በአካባቢው በሚገኝ ወንዝ በቦረቦረው ጉድጓድ ውስጥ ጣላት።

ድርጊቱ እንደተሰማ የአቶ ለቴቦ ቤተሰብ በሀዘን ተመትቶ እርር ኩምትር አለ። በአካባቢው እረኞች ጥቆማ የተገኘውን የመካሜን አስከሬን አንስተው በባህላቸው መሠረት የቀብሯን ሥነ ሥርዓት ቢፈጽሙም መሪሩ ሀዘናቸው ከልባቸው ሊወጣ ከቶውንም አልቻለም ነበር። ምሥጢሩ ውሎ ያደረው ለጥቂት ቀናት ብቻ ስለነበር ገዳዩ ማቴዎስ መሆኑ ተረጋገጠ።

ጉዳዩ በቸልታ ሊታለፍ የሚገባው ስላልነበር የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች በእርቀ ሰላም ለመፍታት ምክክር ጀመሩ። የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች በሽማግሌዎቹ ፊት ቀርበው በሞቀው ጉርብትናቸው መካከል የገባው ነፋስ ምክንያቱ ምን እንደነበረ በዝርዝር አስረዱ። ይህ ለረጅም ጊዜ ሳይፈታ የቆየው የሁለቱ ጎረቤታማቾች ቂምና ቁርሾ ጉዳዩ ጭርሱኑ በማይመለከታት ታዳጊ ንጹሕ ደም መደምደሙ የባሰ ቁርሾውን ሊያባብስ እንደሚችል የተረዱት ሽማግሌዎች “በደም ማድረቂያው ዘዴ” ጉዳይ ላይ አብዝተው መወያየት ቀጠሉ።

በቀሉ መቀጠል ስለማይገባው ሽማግሌዎቹ በአቶ ለቴቦ ላይ እንደ እሬት የሚመር፣ እንደ መርግ የሚከብድ ውሳኔ በማሳለፍ በተግባር እንዲፈጽሙ ግድ አሏቸው። “ከፊተኛው የኋለኛው” እንዲሉ ለሰላም ሲባል መከራ በተሸከመው ቤተሰብ ጫንቃ ላይ ሌላ ቋጥኝ ጫኑባቸው።

በውሳኔው መሠረትም አቶ ለቴቦ የልጃቸውን የመካሜን ገዳይ ማቴዎስን ልክ ለሟች ልጃቸው እንደሚያደርጉት ለቀናት አቅፈውት እንዲያድሩ ተበየነባቸው። ደመኛውን ወጣት ልክ እንደ ወለዱት ልጅ የፍቅር ጠረን እየሰጡ አቅፎ በመተኛት የተፈጸመው የባህላዊው እርቀ ሰላም እጅግ የሚከብድ ቢሆንም የሁለቱን ቤተሰብ ጉርብትናና መልካም ወዳጅነት “በይቅር ለእግዚሃር” አጠናከረው እንጂ ከነቂማቸው እንዲኖሩ አላደረጋቸውም። የመፈዋወስ መድኃኒት ሆናቸው እንጂ ቁርሾውን እያመነዠጉ እንዲኖሩም አላደረጋቸውም። እስከ ደም ማፍሰስ የተፈጸመን ድርጊት በእርቀ ሰላም ለመፍታት ይህ ታሪክ ሁነኛ ማስተማሪያ ሊሆን ይችላል።

ኢትዮጵያም በደቡብ አፍሪካው የሰላም ንግግር ያሸነፈችው በተመሳሳይ ውሳኔ እንጂ ፖለቲካውና ዲፕሎማሲው ብቻ በተጫወቱት የአሸናፊነት ሚና አይደለም። በፍጹም። ታላቋ ኢትዮጵያ “ዕርቅ ደም ያድርቅ” ብላ ግፍ የፈጸመባትን ቡድን ለማቀፍ የጨከነችው ባህሏም ታሪኳም የከበረ ስለሆነ ነው። ይህ ልበ ሰፊነቷና አሸናፊነቷ ለአህጉረ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለግዙፏ ዓለማችንም ታላቅ ትምህርት እንደሚሆን ይታመናል። “ዕርቅ ደም ያድርቅ” ይሏ እንዲህ ነው። ሰላም ይሁን።

# የሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ማነቆዎች

ምሕረት ሞገስ



በሲምፖዚየሙ ላይ የህብረት ሥራ ዩኒየኖች፣ የፌዴራል ኮሚሽንና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች፣ ተገኝተዋል፤

ዩኒየኑ ከአስራ አምስት አገራት ያላነሱ ደንበኞች አሉት። በተለይ በማርና ቡና ታዋቂነትን ያተረፈ እና በአገር ውስጥም ቡናው የተለመደና የታወቀ ነው፤ የቤንች ማጂ ጫካ ቡና ህብረት ሥራ ዩኒየን። የዩኒየኑ የምርት ዝግጅት ሥራ ክፍል ዳይሬክተር አቶ አብዮት ዳዲ፤ ዩኒየኑ በውጪ ገበያው ላይ ተገቢውን ተሳትፎ እንዳያደርግ የተገደበበት ሁኔታ እንዳለ ይጠቁማሉ። ለእዚህ ምክንያት ከሆኑት መካከል አርሶ አደሩ ምርት በጥራት እንዲያቀርብ የሚያግዘውን ግብዓት ማግኘት አለመቻል አንዱ ነው ይላሉ።

በቅርቡ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ ዞን ሚዛን አማን ከተማ በሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች የገበያ ተሳትፎ ላይ የህብረት ሥራ ዩኒየኖች እና የኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኮሚሽን የስራ ሃላፊዎች በመከሩበት ሲምፖዚየም ላይ የተሳተፉት አቶ አብዮት፣ በምርት ላይ የሚታየውን የጥራት ችግር ለማቃለል በ2014 ዓ.ም ዩኒየኑ የጥራት ማስጠበቂያ ግብዓት ከውጪ ማስገባት መጀመሩን ይጠቅሳሉ።

የምርት ጥራት ግብአቱን በማስገባቱ ወቅት ትልልቅ ፈተናዎች ማጋጠማቸውን አቶ አብዮት ይናገራሉ። የጥራት ማስጠበቂያው በሚፈለግበት ጊዜ መጥቶ ለአርሶ አደሩ እንዲዳረስ ማድረግ እንዳልተቻለም ጠቅሰው፣ ይህም አርሶ አደሩና ዩኒየኑ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ይላሉ። ይህ ችግር ተቃሎ የቡና ማድረቂያ እና ጥራት ማስጠበቂያ ሸቦዎች እና ሸራዎች ቀጥታ ከውጪ እንዲያስገቡ እና በጊዜ አርሶ አደሩ ጋር እንዲደርስ የሚችሉበት ሁኔታ ቢፈጠር እና ድጋፍ ቢደረግ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ያመላክታሉ።

እንደ አቶ አብዮት ገለፃ፤ አካባቢው በጣም ትልቅ የማምረት አቅም አለው። አሁንም ለሀገሪቱ በርካታ ዶላር እያስገባ ይገኛል። በ2013 ዓ.ም አካባቢው ከአንድ ሚሊየን ዶላር ያላነሰ የውጭ ምንዛሬ ማስገባት ችሏል። በዩኒየኑ በወቅቱ ከ150 ኮኒቴነር በላይ ቡና ወደ ውጪ መላክ ተችሏል፤ በ2014 ዓ.ም በተከሰተው አገራዊ ችግር እና ዩኒየኑም ባጋጠመው መሰናክል ሳቢያ ወደ ውጪ የሚላከው ምርት መጠን ቀንሷል። አሁን የሚላከውን መጠን ወደ ነበረበት ለመመለስ ታቅዷል። በዚህም ወደ 30 ኮንቴነር የታጠበ፣ 70 ኮንቴነር ደረቅ ቡና ለማቅረብ እየተሰራ ነው።

በዩኒየኑ ውስጥም አለመግባባት ተከስቶ እንደነበር አስታውሰው፣ በገቢዎች በኩል «የተጠራቀመ ያልተከፈለ ግብር አለ» በሚል የዩኒየኑን የባንክ ሂሳብ ገቢዎች ማሳገዱ በ2014 ዓ.ም ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት ከሆኑት መካከል እንደሚጠቀስ ያመለክታሉ።

« ከግብር ጋር ተያይዞ መጥራት ያለባቸው ነገሮች መጥራት አለባቸው። በተለይም ለጥያቄዎች በሰዓቱ ተገቢው ምላሽ ሊሰጥ ይገባል።» የሚሉት አቶ አብዮት፤ «የአስራ አምስት እና የአስራ ሶስት ዓመት ግብር አለብህ።» ብሎ ዩኒየኑ ያልሰበሰበውን ግብር መጠየቁ ዩኒየኑን ብቻ ሳይሆን አርሶ አደሩንም መጉዳቱን ያስረዳሉ።

ይህን ችግር ለመፍታት የተደረገውን ጥረት ተከትሎም ህብረት ሥራ ኮሚሽን እና ግብርና ባለበት ከግብር አስከፋዩ ጋር ድርድር በማድረግ ተጠራቀመ የተባለው የግብር ዕዳ መሰረዙን ጠቅሰው፣ እነዚህን ጥረቶች ተከትሎም የአርሶ አደሩም ሆነ የዩኒየኑ የሥራ ፍላጎት እየተሻሻለ መምጣቱን ተናግረዋል፤ አሁንም መጥራት ያለበት ነገር መጥራት አለበት ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በቀጣይ ተመሳሳይ ነገሮች እንዳይኖሩ ከስር ከስር መከናወን ያለባቸው ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸውም ነው ያመለከቱት።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ዩኒየኑ ምርቱን መጀመሪያ ከአርሶ አደር ማህበራት ይሰበስብና ይሸጣል፤ ሽያጭ ፈጽሞ ካተረፈው 30 በመቶውን ለመሰረታዊ ማህበራት ይሰጣል፤ መሰረታዊ ማህበራት ደግሞ ለአርሶ አደር ያከፋፍላሉ። በዚህ መልኩ ሲከፋፈል አርሶ አደሩ ከሚደርሰው ገንዘብ ላይ አስር በመቶውን ግብር ይከፍላል። አርሶ አደሩ ራሱ ግብር እየከፈለ፤ አሁን በድጋሚ ዩኒየኑ ይክፈል እየተባለ መሆኑን በመጠቆም፤ ጉዳዩ ተገቢነት የጎደለው ስለመሆኑ ያብራራሉ።

ዩኒየኑ ግብር መክፈል ካለበት በወቅቱ ተነግሮት መስተካከል ያለበት ጉዳይ ባለመስተካከሉ የተነሳ ዩኒየኑ በ2014 ዓ.ም ምርት መሰብሰብ አልቻለም ነበር ያሉት አቶ አብዮት፣ አሁንም ገቢዎች አካባቢ ጥርት ያለ ስራ ቢሰራ ለውጥ እያመጣ ከሳር ቤት ወደ ቆርቆሮ ቤት እየተሸጋገረ ያለው አርሶ አደር የበለጠ የዕለት ገቢው ሊያድግ ይችላል ሲሉ ያብራራሉ።

አሁን እያንዳንዱ አርሶ አደር ያቀደውን በደንብ ተረድቶ እየሠራ ነው ያሉት አቶ አብዮት፣ ዩኒየኑ በ2013 ዓ.ም 150 ኮንቴነር ቡና ወደ ውጪ ልኳል ይላሉ። በ2014 ዓ.ም ግን ብዙ እንዳልተሳካለት ጠቅሰው፣ በዚህ ዓመት ግን 12 ሚሊየን ኩንታል እሸት ቡና ለመሰብሰብ ማቀዱን ተናግረዋል። አሁን የቡና መሰብሰቢያው ወቅት ገና መሆኑን ገልጸው፣ እስከ አሁን ብዙ ባይሰበሰብም እስከ ታህሳስ ሁሉንም መሰብሰብ ይቻላል ብለው እንደሚያምኑ አስታውቀዋል።

ሌላው የሲምፖዚየሙ ተሳታፊ የኦሮሚያ ቡና አምራች ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ነው። በዩኒየኑ የዋንኮ ቡና የማርኬቲንግ ባለሞያ አቶ ኩመራ አሸናፊ እንደሚናገሩት፤ ዩኒየኑ በኦሮሚያ ክልል የሚመረቱ ቡናዎችን «ዋን ኮ ቡና» የሚል መለያ (ብራንድ) በመያዝ የተቆላ፣ የተፈጨ እና ጥሬ ቡና ወደ ውጪ ይልካል። ለአገር ውስጥ ገበያም ያቀርባል። በዩኒየኑ የይርጋጨፌ፣ የጉጂ፣ የሊሙ፣ የጅማ፣ የሐረር እና የነቀምት ቡናዎች ለገበያ ይቀርባሉ። ለውጪ ለመላክ የማይመጥኑትን ደግሞ ቆልቶና ፈጭቶ ለአገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል።

ድርጅቱን ለየት የሚያደርገው ጥራት መሆኑን በማመላከት፤ የቡናን ጥራት ለማስጠበቅ ከገበሬው ጀምሮ የሙያ ድጋፍ በመስጠት እስከ መጨረሻው ሒደት የሙያ ክትትል እና ድጋፍ እንደሚደረግም ይገልፃሉ። ዩኒየኑ ይህንን ጠብቆ ምርት ስለሚሰበስብ በብዛት ምርጥ ቡና ያቀርባል ሲሉ ያብራራሉ።

አቶ ኩመራ እንደሚገልፁት፤ የኦሮሚያ ቡና በትላልቅ ገበያዎች ላይ በጥራቱ ይታወቃል። በውጪ ገበያም ምንም ሳይቀላቀልበት በላከው ናሙና መሰረት እንደሚሸጥ ይታወቃል። ይህ ዩኒየን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታወቀው በላይ በውጪው አለም በደንብ የታወቀ ነው። ትልልቅ የቡና አቅራቢ ድርጅቶች ስታር ባክስን ጨምሮ የሚመርጡት ትልቅ ኩባንያም ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በዋንኮ ቡና ታዋቂነትን እያተረፈ ይገኛል።

በአገር ውስጥ ቡና ተቆልቶ የተፈጨ ቡና ይቀርባል ሲባል ከገብስ ጋር የሚተሳሰርበት ሁኔታ ነበር የሚሉት አቶ ኩመራ፣ ዋንኮ ግን ንፁህ ያልተቀላቀለ ቡና በማቅረብ ተለይቷል ነው የሚሉት። ጥራትን ትኩረት አድርጎ የሚሰራ እና አንዱ ቡና ከሌላው ቡና እንደሚለይ ማሳየቱን ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህ ዩኒየን ጥራትን አስጠብቆ ምርት ሲያቀርብ በምቹ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አይደለም፤ በቡና ላይ ያለው የኮንትሮባንድ ንግድ የቡና ንግዱን እየረበሸበት ይገኛል። በአጠቃላይ በወጪ ንግድ ላይ በህጋዊ መንገድ ከሚወጣው ይልቅ በኮንትሮባንድ የሚወጣው ቡና እየበዛ ነው። ይህ በመንግስት ክትትል መቆም ይኖርበታል፤ ያለበለዚያ አርሶ አደሩ እና ዩኒየኖች ተጎጂ መሆናቸው አይቀርም።

የተለያዩ ሌሎች ሴራዎችም መኖራቸውን የሚገልፁት አቶ ኩመራ፤ ለገበሬውም ሆነ ለአገር የማያስቡ ለውጭ ምንዛሬ ፍለጋ ብቻ ብለው ቡና የሚልኩ መኖራቸውንም ይጠቁማሉ። ወደ ውጪ የሚላከው ቡና ከአገር ውስጥ ባነሰ ዋጋ ለገበያ የሚቀርብ ሲሆን፤ ግለሰብ ቡና ላኪዎች በዚህ የሚያጡትን በተለያየ መንገድ የሚያካክሱበት ሁኔታ እንዳለ ይጠቁማሉ። አገር ውስጥ በውድ ገዝተው በውጪ ሀገር ሸጠው በሚያገኙት ዶላር ብዙ የሚያተርፉበትና ህዝቡን መልሰው የሚጎዱበት ሁኔታ ስለመኖሩ ያብራራሉ። የቡና ዋጋ በአገር ውስጥ ገበያ ጨመረ ሲባል ለገበሬው ትልቅ ጥቅም ሊመስል እንደሚችልም አመልክተው፣ ይህ ችግር የኢትዮጵያን የቡና የወጪ ንግድ እየረበሸው መሆኑን ይገልፃሉ።

እንደ አቶ ኩመራ ገለጻ፤ ለግለሰብ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለአገርም ማሰብ ያስፈልጋል። ቡናውን በውድ ገዝተው በውጪ ገበያ አራክሰው ሸጠው፤ ጥራቱን ያልጠበቀ ዘይትና ብረት አስገብተው ህብረተሰቡ ላይ መልሰው ዋጋውን ይጭናሉ። በዚህ ሳቢያ በጥቂት ግለሰቦች አገር ብዙ ታጣለች። ከግል ጥቅም ይልቅ የአገር ጥቅም ላይ ቢታሰብበት መልካም ነው።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የቤንች ሸካ ዞን የቤንች ማጂ አንድነት የገበሬዎች ሁለገብ ህብረት ሥራ ዩኒየን የቡና እና የቅመማ ቅመም የምርት ጥራት ባለሙያ ወይዘሮ ራዲያ ጀማል በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ መሰረታዊ ማህበሩ ከአርሶ አደሩ የሰበሰበውን ምርት ዩኒየኑ ሰብስቦ ገበያ አፈላልጎ ይሸጣል። ቡና በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪ ገበያም ይሸጣል። ዩኒየኑ ቡና ላይ ብዙም የገበያ ችግር የለበትም።

እሳቸው እንዳሉት፤ ዩኒየኑ ኮረሪማ ላይ ከፍተኛ ችግር አጋጥሞት ነበር። መሰረታዊ ማህበሩ ከአርሶ አደሩ ከሰበሰበ በኋላ ዩኒየኑ ተረክቦ ገበያ ሲያፈላልግ የኮረሪማ ገበያ ጠፋ። በዚህ ምክንያት በአንድ ዓመት ውስጥ ዩኒየኑ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊየን ብር ከስሯል።

በሌላ በኩል ለዩኒየኑ አባላት ስልጠና በመስጠት የማድረቂያ ሸቦ መቅረቡን ወይዘሮ ራዲያ ጠቅሰው፣ የቡና ማድረቂያ ሸቦ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉም ያስገነዝባሉ። አሁን አርሶ አደሩ ስለጥራት ብዙ ችግር የለበትም፤ በተሻለ ጥራት ሲያቀርብ የተሻለ ገንዘብ እንደሚገኝ ተረድቷል የሚሉት ባለሙያዋ፣ ፈተና እያጋጠመ ያለው ከቡና ውጪ ባሉት ምርቶች ገበያ ማጣት ነው ይላሉ።

የፌዴራል ሕብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ዑመር እንደተናገሩት፤ የቡና አምራች ህብረት ሥራ ማህበራት ወደ ውጪ የሚልኩት የቡና ምርት አነስተኛ ነው፤ አሁን ደግሞ የበለጠ እየቀነሰ መጥቷል። ለዚህ ችግር መንስኤ የሚሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ የአገር ውስጥ ገበያ በውጪ ገበያው ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ ህብረት ሥራ ማህበራት ጥራት ያለው ምርት ይዘው አለመገኘታቸው፤ ምርቱን በሚሰበስቡበት ወቅት የሚያስፈልጋቸው በቂ ፋይናንስ ማግኘት አለመቻላቸው ከምክንያቶቹ መካከል ተጠቃሾቹ ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ማህበራት፣ ዩኒየኖች፣ ባንኮች እና ከሚሽኑ በትኩረት መስራት አለባቸው።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ አክሊሉ ተገኝ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ በክልሉ 2ሺ 369 የህብረት ሥራ ማህበራት እና 20 ዩኒየኖች ይገኛሉ። ዩኒየኞቹ የሚጠበቀውን ያህል ወደ ውጪ በሚላኩ ምርቶች ላይ ስኬታማ አይደሉም፤ የዚህ ምክንያቶቹ ደግሞ የውስጥና የውጪ ተብለው የሚታዩ ናቸው።

በተለይ በቡና ንግድ ሥራ ላይ የተመሰረቱ ማህበራት ዋነኛ ችግራቸው የፋይናንስ ችግር ነው። ዩኒየኖች አብዛኛውን ከአባላት የሚቀበሏቸውን ምርቶች ለመሰብሰብ ግለሰቦች ገንዘብ ይፈልጋሉ። ዩኒየኖች ደግሞ ለግለሰቦቹ ገንዘብ ማቅረብ አይችሉም። ከባንክ በብድር መልክ የሚገኘው አብዛኛው የግብይት ገንዘብ የሚለቀቀው መጨረሻ ላይ ምርቱ ተሰብስቦ ለገበያ ቀርቦ ግብይቱ ሊያልቅ ሲል ነው። ስለዚህ በተለይ የፋይናንስ ተግዳሮት የዩኒየኞቹ ከፍተኛ ችግር ነው።

ማህበራት እና ዩኒየኖቹ ያላቸውንም ገንዘብ የሚያስተዳድሩበት መንገድም የራሱ ተግዳሮት ያለበት መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ የሚያገኙትን ፋይናንስ ለዋናው ተልዕኳቸው ከማዋል ይልቅ ወጣ ያለ ተግባር ላይ ሲያውሉ መታየቱንም ያመለክታሉ።

ይህን ችግር ለማቃለል ክትትል እና ድጋፍ እየተደረገ መሆኑንም አቶ አክሊሉ ይገልጻሉ። የሕብረት ሥራ ማህበራትን በተለይ ከቡና አንፃር እየፈተናቸው ያለው የተጋነነ ዋጋ መሆኑንም ይጠቅሳሉ።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ አሁን በሸካ አንድ ኪሎ እሸት ቡና እስከ ሃምሳ ብር እየተሸጠ ነው። ይህም በዓለም አቀፍ ግብይት ደረጃ በዶላር ሲሰላ አሁን ላይ አንድ ኪሎ እሸት ቡና በዓለም ገበያ ላይ አራት ዶላር ነው። አሁን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ሸካ አካባቢ አንድ ኪሎ ቡና እየተሸጠ ያለው በ6 ዶላር ነው። የአስተዳደር ወጪ፣ የትራንስፖርት ወጪ ሳይጨመር ይህ ዋጋ እጅግ የተጋነነ ነው።

ይህ ሁኔታ ሲታይ የሕብረት ሥራ ማህበራት በግለሰብ ነጋዴዎች ምክንያት ከወጪ ንግድ አቅራቢነት ሊወጡ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው። በዛ ላይ ማህበራቱ ግብይቱን ለመፈፀም የፋይናንስ ችግራቸውን ለማቃለል ቅድመ ብድር ይዘጋጅ ቢባልም፤ ብድሩ የሚለቀቀው ግብይቱ ካለቀ በኋላ መሆኑ ግለሰብ ላኪዎች ተፎካክረው ቀድመው የሚወስዱበትን ሁኔታ በስፋት ፈጥሯል። ስለዚህ ጉዳዩ አገራዊ መፍትሔ፤ በተለይ የፖሊሲ አቅጣጫ ይፈልጋል ሲሉ የችግሩን አሳሳቢነት አስረድተዋል።

ከግብር ጋር ተያይዞ የተነሳውን ጥያቄ በሚመለከት በሰጡት ምላሽም፤ ግብር ላይ መጣረሶች መኖራቸው እንደማይካድ ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በህብረት ሥራ አዋጅ የሚወጣው የሚፀድቀውም በግብር መስሪያ ቤት የሚወጣውም የሚፀድቀውም ተመሳሳይ በሆነ አካል ነው። ህጉ ተናቦ መውጣት አለበት። ተናቦ ባይወጣ እንኳ ተናቦ ከመስራት አንፃር ሰፊ ክፍተት አለ ሲሉ ያብራራሉ።

ግብር እንዴት እና መቼ መከፈል አለበት? የሚለውን ለማህበራት የማሳወቅ ሥራ አልተሠራም። ግብር መክፈል ካለባቸው ግብር መክፈል አለባቸው ብለን እናምናለን ያሉት አቶ አክሊሉ፣ ለበርካታ አመታት የተጠራቀመ ብሎ መጠየቅ የለበትም ይላሉ። ለአስር እና ለአስራ ሶስት ዓመታት ቆይቶ መጠየቅ ተገቢ እንዳልሆነም አመልክተዋል። እዚህ ላይ መነጋገር ይገባል ይላሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ አምና የተፈጠረውን ችግር ለጊዜው መፍታት እንደታቻለም አስታውሰው፣ በቀጣይ ነገሮችን ማስተካከል እንደሚገባ አያጠያይቅም፤ ለዚህም ከግብር አስከፋዩ ጋር እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የጫኝና አውራጆች ውንብድና እስከ መቼ?

**ዋለልኝ አየለ**

ከሁለት ሳምንታት በፊት በማኅበራዊ ገጾች አንድ አስገራሚ መረጃ ሲዘዋወር ነበር። ከሆነ ሆስፒታል አስከሬን ሲወጣ ጫኝና አውራጆች እኛ ነን የምንጭነው ብለው ግርግር ተፈጥሮ ነበር የሚል። ከዚያ በፊት ደግሞ አውቶብስ ተራ የሆነች እናት ልጇን ከጀርባዋ ላይ ካላወረድንልሽ አሉ ተብሎ በቀልድም በቁም ነገርም ሲወራ ነበር።

እነዚህ አጋጣሚዎች በአጋጣሚ የተከሰቱ ናቸው ወይም የችግሩን አሳሳቢነት ለመግለጽ የተጋነኑ ናቸው እንበል፤ ግን በገሃዱ በራሳችን ዓይን ያየናቸው ክስተቶች ራሱ ከዚህ ብዙም የተለዩ አይደሉም።

2011 ዓ.ም ሰኔ ወር አካባቢ ነው። አንድ ጓደኛዬ ኮዬ ፈጬ ቤት ተከራይቶ ዕቃ ጭነን ሄድን። ዕቃው ከእኛ የሚያልፍ አይደለም። ልክ ገና መኪናው ሲደርስ ከአካባቢው ነዋሪ በላይ የሚሆኑ ጫኝና አውራጆች ከየሥርቻው ተንጋግተው መጡ።

ማንንም ሳያናግሩ እየዘለሉ መኪናው ላይ መውጣትና መፍታት ጀመሩ። ጓደኛዬ በከፊል ነገሩን ያውቅ ስለነበር ማባበልና መለማመጥ ጀመረ፤ እኔ ስለማላውቅ፣ ሲጀመር እኛ አውርዱልን ሳንል ለምን መፍታት ጀመሩ ብየ ስገረምና ስቆጣ እኔን እያስረዱ አረጋጉኝ።

ልጆቹ ዕቃውን አውርደው የትኛው ቤት እንደሆነ ብቻ አሳዩን ነው ያሉት። ያለማንም ፈቃድ ራሳቸው አወረዱት፤ አስገቡት።

አናዳጁ ነገር ይህ አይደለም፤ ዋጋ የጠየቁት ዕቃውን ካወረዱ በኋላ መሆኑ ነው። የጠየቁት ገንዘብ ዕቃው ራሱ ቢሸጥ አያወጣውም። በቀልድም በቁም ነገርም በቁጣም ብንነግራቸው አልሰሙም፤ እንዲያውም ነገሩ ወደሌላ (የብሔር መልክ ያለው) ነገር እንደሚሄድ አስፈራሩን። የዚህን ጊዜ ታግሶ የቆየው ጓደኛዬም ያመጣችሁትን አምጡ አልከፍልም ብሎ ተቆጣ። የአካባቢው ሰውና ዕቃውን ያደረሱልን ሾፌር (ሽማግሌ ናቸው) በብዙ ማግባባት አግባቡንና ጣጣው አለቀ።

በኋላ የአካባቢው ሰዎች ሲነግሩን በዚህ ምክንያት ብዙ አይነት ጥፋቶች ደርሰው እንደነበር ገጠመኞችን ነገሩን። መገናኛ ከቤልቪው ሆቴል ከፍ ብሎ ባሉ መንደሮች ውስጥ አንድ ግለሰብ አልከፍልም ብሎ የደረሰበትን ጉዳት በዚያው ሰሞን ሰማሁ።

በአጠቃላይ በጫኝና አውራጆች ምክንያት የተፈጠሩ ጥፋቶች ይቆጠሩ ቢባል ሰልፍ ራሱ የሚያስወጡ ናቸው። ከላይ የገለጽኳቸው ገጠመኞች በጣም ቀላል የሚባሉት ናቸው። ለሕክምና ወይም በስደት የመጡ መንገደኞች መናኸሪያ ዙሪያ ሲያለቅሱ ማየት የየዕለት ክስተት ሆኗል። ለፌስታል ቁጥራት እና ለትንንሽ ቦርሳዎች ሳይቀር ኩንታል ጤፍ የሚገዛ ዋጋ ይጠይቋቸዋል። ‹‹ይህ እኮ እኔ ራሴ መያዝ የምችለው ነው›› ሲሉ ከእጃቸው ላይ ቀምተው ይይዙታል። ምክንያታቸው ደግሞ ተደራጅተን የምንሠራ ስለሆነ ማንም ሰው የትኛውንም ዕቃ በእኛ በኩል ነው መጫንና መውረድ የሚችል ብለው ነው የሚያምኑት።

በዚሁ በጫኝና አውራጅ ምክንያት የሰው ሕይወት ሁሉ አልፏል። እጅግ አሳሳቢ ከመሆኑ የተነሳ በዚሁ በጫኝና አውራጅ ጉዳይ ላይ በሚያዚያ ወር መጨረሻ አካባቢ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በውይይቱ ላይም በጫኝና አውራጆች የደረሱ ጥፋቶችን የሚያሳይ ጽሑፍ ቀርቦ ነበር።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የማኅበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ዳይሬክተር ኮማንደር ሰለሞን ፋንታሁን ራሳቸው ‹‹ባለንብረቶች እቃው ከተገዛበት በላይ የተጋነነ ዋጋ እየተጠየቁ ነው›› ብለው ነበር። ፖሊስ ጠንካራ እርምጃ እንደሚወስድም አሳስበው እንደነበር አስታውሳለሁ።

እንግዲህ ችግሩ እዚህ ድረስ አሳሳቢ ሆኗል ማለት ነው። ምናልባትም ሌሎች ወቅታዊ ሀገራዊ ውጥረቶች ስለነበሩ የመገናኛ ብዙኃኑም ያን ያህል ትኩረት አልሰጡትም እንጂ የጫኝና አውራጆች ነገር በጠራራ ፀሐይ ዝርፊያ እየሆነ ነው። የተፈጠረው ችግር አጀንዳ የሚሆነውም ችግሩ የደረሰበት ሰው የተማረ ወይም ታዋቂነት ያለው ሲሆን ነው። ያጋጠመውን ነገር ወደ አደባባይ ማውጣት የሚችል ሲሆን ነው።

ነገሩን ወደ አደባባይ ማውጣት የማይችሉና ከሀገር ቤት የሚመጡ ብዙ ወገኖች ብዙ አይነት ስቃይ ደርሶባቸዋል። እነዚህ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ የሚመጡት ለመዝናናት አይደለም፤ በሆነ አስቸኳይ ምክንያት ነው። በእንዲህ አይነት ምክንያት የሚመጡ ደግሞ ትርፍ ገንዘብ አይዙም። ምናልባትም ለትራንስፖርት እና ለመጡበት ጉዳይ የተቆጠረ ገንዘብ ብቻ ሊይዙ ይችላሉ። እነዚህን ሰዎች ነው ትንንሽ ከረጢት ሁሉ ሳይቀር ለአገር አቋራጭ ጉዞው ከከፈሉት በላይ የሚጠይቋቸው።

ይህን የአደባባይ ውንብድና ሁላችንም ልንታገለው ይገባል፤ በእኔ ካልደረሰ... በሚል ማለፍ የለብንም። ለዚህ ሥራ ደግሞ ፖሊስ ተባባሪ መሆን አለበት። ልክ ባለፈው ሳምንት ጽሑፋችን ፖሊስ ለሚሠራቸው አኩሪ ሥራዎች እንዳመሰገነው ሁሉ ቅሬታዎች ሲኖሩም እንወቅሳለን። ብዙ ጊዜ የሚነሳው ቅሬታ ለፖሊሶች ስንነግራቸው ‹‹ሥራቸው ነው›› እያሉ ችላ ይሏቸዋል የሚል ነው። አንዲትን ከገጠር የመጣች ምስኪን ለፌስታል ዕቃ ብዙ ብር ሲጠይቁ ፖሊስ ዝም ሊል አይገባም፤ ምክንያቱም ይህ ከዝርፊያ አይተናነስም።

የተጋነነ ዋጋ መጠየቃቸው ብቻ አይደለም ችግሩ። በሚፈጠረው ግርግር በዕቃ ላይ ጉዳት እየደረሰ ነው። በተለይም ተሰባሪ ዕቃዎች በመጓተት ጉዳት ይደርስባቸዋል። መንገደኛው ‹‹ራሴው መያዝ የምችለው ነው››ሲል ጫኝና አውራጆቹ በኃይል ለመንጠቅ ይሞክራሉ፤ ይህኔ ዕቃው ይጎዳል፤ ባለንብረቶቹ አቅመ ደካማ ከሆኑ ደግሞ አካላዊ ጉዳትም ይደርሳል ማለት ነው።

ከዓመታት በፊት እንደማውቀው አንድ ሰው ዕቃ የሚያስጭነውና የሚያስወርደው በራሱ ፈቃድ ነበር። እንደ ሻንጣ እና የፌስታል ዕቃዎች ደግሞ ማሸከም ከፈለገ ተሸካሚ ራሱ ባለንብረቱ ጠርቶ ነው። ወይም ተሸካሚዎች ጠጋ ብለው በትህትና እና በልመና አይነት ‹‹ጋሼ ልሸከመው?›› ብለው ነው። ይህኔ ሰውየው በሰብዓዊነት (ለተሸካሚ ልጆች ሲል) ወይም መያዝ ስላልተመቻቸው ያስይዛቸዋል። ብር የሚሰጣቸው እንኳን ባለንብረቱ የፈቀደውን ነበር። ‹‹ስንት ነው?›› ሲላቸው በትህትና ‹‹አንተ የፈቀድከውን›› ይላሉ። የሰጣቸው ትንሽ ሆኖ ቅር ቢላቸው እንኳን ‹‹ኧረ ጋሼ ሩቅ እኮ ነው›› ይላሉ፤ ወይም በቂ ነው ካሉ በትህትና አመስግነው ይሄዳሉ።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ውንብድና ሆነ! ይሄ ደግሞ እልህ ያጋባል። ባለብንረቱም ‹‹እንዲያውም ራሴ ነኝ የምሸከመው!›› በማለት ወደ እልህ ውስጥ ይገባል። በመተሳሰብ መሆን የነበረበት ነገር ወደ መጨቃጨቅ ሲሄድ ግርግሩ ለአካባቢው ሁሉ ይተርፋል ማለት ነው።

አሁን ተስፋችን ያለው ፖሊስ ላይ ነው። ፖሊስ ለተወሰነ ጊዜ ከልቡ ቢሠራ የሚቸገረው ለትንሽ ጊዜ ነው፤ ከዚያ በኋላ ስለሚፈሩ ልክ ይገባሉ። ሙሉ ሥራቸውን ላለማጣት ሲሉ ሥርዓታቸውን ይዘው ይሠራሉ። ስለዚህ ይህ ችግር መስመር እስከሚይዝ ፖሊስና ሕዝቡ ተባብሮ ሊሠራ ይገባል።

# ዓለም አቀፍ

## ሶማሊያ ታጣቂው ቡድን “አል ሻባብ” በሚለው ስያሜ እንዳይጠራ አገደች



የሶማሊያ መንግሥት የሃይማኖት ጉዳዮች ሚኒስቴር በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሰው ታጣቂ እስላማዊ ቡድን “አል ሻባብ” በሚለው ስሙ እንዳይጠራው ክልከላ ጣለ። የታጣቂው ቡድን መጠሪያ “አል ሻባብ” የአረብኛ ስያሜ ሲሆን ትርጉሙም “ወጣቶቹ” የሚል ነው። መነሻውን የሶማሊያ አድርጎ በጎረቤት ሀገራት ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ቡድኑ በአሸባሪነት የተፈረጀ ነው።

የሶማሊያ መንግሥት ቡድኑን ለማዳከም ከፍተኛ ዘመቻ እያካሄደ ሲሆን፣ የቡድኑን ተቀባይነት ለመቀነስም የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። የሀገሪቱ የሃይማኖት ጉዳዮች ሚኒስቴር ታጣቂው ቡድን አልሻባብ አስካሁን ሲጠቀምበት የነበረውን ስያሜ ከማገዱ በተጨማሪ፣ ሕዝቡ ቡድኑን “ካህዋሪጅ” ብሎ እንዲጠራው ጠይቋል። ይህ ስያሜ ከእስልምና ያፈነገጠ ቡድን መጠሪያ ሲሆን፣ በበርካታ ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የሚያሳጣ ነው።

በተጨማሪም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባወጣው መግለጫ ላይ ማንኛውም የሃይማኖት መሪዎች ከአልሻባብ ጋር ግንኙነት ካላቸው ታጣቂዎች ጋር ስምምነትም ሆነ ግንኙነት እንዳያደርጉ ክልከላ ጥሏል። የሶማሊያ መንግሥት እንዳለው አዲስ በወጣው መመሪያ አል ሻባብ “ካህዋሪጅ” በሚል መጠሪያ የተሰየመው በቡድኑ ላይ በከፈተው ዘመቻ አማካይነት ነው።

ይህ በሶማሊያ መንግሥት አማካይነት ለታጣቂው የአል ሻባብ ቡድን አዲስ አይነት ስያሜ ሲሰጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። ከሰባት ዓመት በፊት ቡድኑን ከሕዝቡ ለመነጠል አዲስ ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። በአውሮፓውያኑ 2015 የሶማሊያ መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን አል ሻባብን “ኡጉስ” በሚል ምህጻረ ቃል እንዲጠሩት ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር። መጠሪያው “የሶማሊያን ሕዝብ የሚጨፈጭፍ ቡድን” ከሚሉት ቃላት የተወሰደ አህጽሮተ ቃል ነው።

ይህንንም ተከትሎ ታጣቂው ቡድን ጋዜጠኞችን ጨምሮ ማንም ሰው የመንግሥትን ትዕዛዝ ተከትሎ ቡድኑን በተባለው ስያሜ የሚጠራ ከሆነ እርምጃ እንደሚወስድ አስጠንቅቆ ነበር። የሶማሊያ መንግሥት በአል ሻባብ ላይ እየወሰዳቸው ካሉት እርምጃዎች መካከል በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ ማንኛውም የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን የቡድኑን እንቅስቃሴ በሚመለከት ምንም አይነት ዘገባ እንዳይሠሩ እገዳ መጣሉ ይታወሳል።

አዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ፣ በታጣቂው ቡድን ላይ ሲካሄድ የነበረውን ዘመቻ የመንግሥት ኃይሎች ከጎሳ ሚሊሻዎች ጋር በመተባበር አጠናክረው ቀጥለዋል። ከአልቃኢዳ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚነገረው አልሻባብ ከሶማሊያ ባሻገር በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ውስጥ በሚፈጽማቸው የሽብር ጥቃቶች የሚወገዝ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

## አሜሪካ ከሩሲያ ጋር አሁንም ምሥጢራዊ የግንኙነት መስመር እንዳላት አመነች



የአሜሪካ የብሔራዊ ደኅንነት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ አማካሪ ጄክ ሰለቨን አገራቸው ከክሬምሊን ጋር ንግግርና ምክክር የምታደርግባት የግንኙነት መስመር እንዳልዘጋች ተናግረዋል። ዋሺንግተንና ሞስኮ የመረጃ ልውውጣቸው በዩክሬን ጦርነት ሳቢያ እንዳልተስተጓጎለ ሚስተር ሰለቨን አረጋግጠዋል።

ሚስተር ሰለቨን በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገሩ ይህ የግንኙነት መስመሩ እንዲቀጥል ማድረግ ‘ከአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅምና ፍላጎት ጋር የሚስማማ’ ነው ብለዋል። የጄክ ሰለቨን ንግግር የመጣው ዋይት ሐውስ ከሩሲያ ጋር ኒውክሌርን በተመለከተ ውስጥ ውስጡን ይነጋገራል የሚል መረጃዎችን አለማስተባበሉን ተከትሎ ነው። ይህን የውስጥ ለውስጥ ንግግር የሚመሩት ደግሞ ጄክ ሰለቨን ናቸው ተብሎ ሲዘገብ ነበር።

በተለይ የዎል ስትሪት ጆርናል ዘገባ ሚስተር ሰለቨን ከሩሲያ አቻቸው ጋር ምስጢራዊ ንግግር ያደርጋሉ ሲል ዘግቦ ነበር። በእርግጥም ጋዜጣው እንደዘገበው ጄክ ሰለቨን ከሩሲያው አቻቸው ኒኮላይ ፓትሮሼቭ ጋር እንዲሁም ከክሬምሊን ከፍተኛ የውጭ ጉዳዮች ረዳት ከሆኑት ዩሪ ኡሻኮቭ ጋር ባለፉት ሰባት ወራት ንግግር ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እንደ ዎልስትሪት ዘገባ ከሆነ እነዚህ የሁለቱ አገራት ከፍተኛ የደኅንነት ኃላፊዎች በዋናነት ውይይታቸው ያጠነጠነው የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ዙሪያ የተደቀነውን አደጋና ፍጥጫ በማስቀረት ዙሪያ ነው።ይሁንና ጄክ ሰለቨን ከዚህ ጉዳይ ውጭ ጦርነቱን በማቆም ጉዳይ ላይ ከክሬምሊን አቻቸው ጋር እንዳልተነጋገሩ ጠቁመዋል።

ባለፈው ወር ሚስተር ሰለቨን በአንድ መድረክ ላይ ሲናገሩ ሩሲያ ኒውክሌር ለመጠቀም ከሞከረች አደገኛና የከፋ ጣጣ ይዞባት ይመጣል ብለው ነበር። የዚህን ጋዜጣ ዘገባ ተከትሎ የክሬምሊን ቃል አቀባይ ‘የምዕራብ ሚዲያ ወትሮም እንቶፈንቶ መዘገብ ልማዱ ነው’ ሲሉ ሪፖርቱን አጣጥለውት ነበር።

ይሁንና ጄክ ሰለቨን አሜሪካ ከሩሲያ ጋር የንግግር መስመሩን ክፍት አድርጋ መቆየትን እንደምትመርጥ ተናግረዋል። የጆ ባይደን ሁነኛ አማካሪ ናቸው የሚባሉት ጄክ ሰለቨን አሁንም ድረስ ከሞስኮ ጋር መነጋገሩ ለአሜሪካም ሆነ በዩክሬን ጦርነት በአንድም በሌላም ሁኔታ ተጽእኖ ላይ ለወደቁ ሀገራት ሁሉ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ባለፈው ሳምንት ዋሺንግተን ፖስት አንድ ከፍተኛ የአሜሪካ ባለሥልጣንን ጠቅሶ እንደዘገበው ኪየቭ ከሩሲያ ጋር በመነጋገሩ ረገድ ግልጽ ልትሆን ይገባል ማለታቸውን አውስቶ እንደነበር ቢቢሲ በዘገባው አውስቷል።

# የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች

**ግርማ መንግሥቴ**



ፕሮፌሰር አለማየሁ ኃይለማርያም ታዋቂውን ጸሐፊ ኒኮላስ ክሪስቶፍ (ማርች 2004)ን ጠቅሰው፤ "አፍሪካ በቀውስ የምትታመስ አህጉር ነች፡፡ ላለፉት አራት አስርት ዓመታት ከጊዜ ወደ ጊዜ ድህነት እየጨመረ የመጣባት፣ በእርስ በእርስ ጦርነት የምትታመስ፣ የዘር ማጥፋት ሰብአዊ ወንጀሎች የሚፈጸሙባት እና አስደንጋጭ የሆነ የሙስና ዘረፋ የሚካሄድባት ብቸኛዋ አህጉር ሆናለች፡፡ አፍሪካ ተስፋ ይኖራታልን?" ያሉትን ጨምሮ ስለ አፍሪካ ብዙ ተብሏል።

በስልጣን ጥም፣ በመፈንቅለ መንግስት ወዘተም ብዙ የተጻፈባት ናት። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁሉ የመስራች አባቶች ራእይም ሆነ ፍላጎት አልነበረም። የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች ፍላጎት የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ሰሞኑን በአይነቱ የመጀመሪያ በሆነው የአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ ላይ ሲናገሩት እንደነበረው የቀደሙ የፓንአፍሪካኒስት አባቶች ራዕይ አንድነት፤ እድገት፤ ብልፅግና፤ ሰላም፤ አፍሪካዊ ወንድማማችነት ... ነበር። ቀስ እያልን ዝርዝሩን እንመለከተዋለን። አሁን ወደ መስራች አባቶች እንሂድ።

ነጮቹ እንደሚመኩባቸውም ሆነ እንደሚኮሩባቸው፣ "ፋውንዲንግ ፋዘርስ" በማለት እንደሚያንቆለጳጵሷቸው ሁሉ፣ ዘመናዊት አፍሪካም መስራች አባቶች አሏት። ለዛውም ከአፍሪካም አልፈው ለአለም የተረፉ። ይሁን እንጂ፣ እንደ እነሱ እኛ አፍሪካዊያን ስናንቆለጳጵሳቸው አይታይም፣ አይሰማም።

ለነገሩ ይህ መፈንቅለ መንግስት የሚሉት ሾተላይ እየደጋገመ በሚመታት አፍሪካ እንዴት ተደርጎ ነው የአሁኑ የበፊቱን የሚያደንቀው፣ እንዴትስ ሆኖ ነው የበፊቱ በአሁኑ የሚወደደው?

የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች፣ አፍሪካን በተመለከተ ሙቱ ቢሏቸው የማይሞቱ፣ ተረሱ ቢሏቸው የማይረሱ ... ናቸው፡፡ ምን ያህል ከጊዜው የቀደሙ እንደሆኑ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ሲያነሷቸው የነበሩ ሀሳቦች፣ ሲያራምዷቸው የቆዩት አቋሞቻቸው፣ ሲያከናውኗቸው የነበሩት ተግባራቶቻቸው ሁሉ ዘመን ተሻጋሪ እንጂ የእለት እንጀራ ብቻ አልነበሩም። በመሆኑም፣ ከትውልድ ትውልድ ሲነሱ፣ ሲወደሱና ሲናፈቁም ጭምር ይስተዋላል። ለዚህ አንድ ጥሩ ማሳያ ቢኖር ሰሞኑን እዚህ አዲስ አበባ የተካሄደው የአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ ነው።

በኢትዮጵያ አነሳሽነትና አዘጋጅነት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ለሶስት ቀናት የቆየውና በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ሲካሄድ የነበረው የአፍሪካ ወጣቶች ጉባዔ ዋና አላማ የፓንአፍሪካኒዝምን እሳቤና ፍልስፍና ለአዲሱ የአፍሪካ ትውልድ ማስተዋወቅና አብሮነትን ማጠናከር ሲሆን፤ በዓለምአቀፍ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ አፍሪካ እንደ አህጉር ያላትን ሚና እንዲጠነክር ለወጣቶች ማሳየት፤ እንዲሁም፣ በአፍሪካ አገራት መካከል የጋራ ትስስርን ማጎልበት ሌላኛው የጉባኤው ዓላማ እንደነበር ሲገለፅ መሰንበቱ ይታወቃል። በአፍሪካ ትብብርና ወንድማማችነት ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የምርምርና ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት እንደ ተደረገባቸውም ታውቋል። በሕይወት የሌሉ የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ታጋዮች (መስራች አባቶች) ቤተሰቦች በጉባኤው ላይ የታደሙ ሲሆን፤ ለታጋዮቹም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አማካኝነት ሽልማት ተበረክቶላቸዋል።

በዚሁ የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባኤ ላይ ከተከናወኑት ተግባራት አንዱ 17 ለሚሆኑ ቀደምት የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ለሕብረቱ ምስረታ እና መጠናከር ላበረከቱት ወደርየለሽ አስተዋፅኦ በቤተሰቦቻቸው በኩል እውቅና መስጠት ሲሆን፤ ከ17ቱ አንዱና ቀዳሚው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ለጠነከረችና ከተፅእኖ ነፃ ለሆነች አፍሪካ ነፃነት እና አንድነት ላበረከቱት አስተዋፆ የተሰጠው እውቅናና ሽልማት ይገኝበታል ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በጉባኤው ማጠቃለያ መርሐ-ግብር ላይ በመገኘት መልእክት ያስተላለፉ ሲሆን፤ የመልእክታቸውም ጭማቂ፤

- አፍሪካውያን ወጣቶች የወደፊቷ አለም መሪዎች ናችሁ፤
- በአህጉሪቱ የሚታዩትን የአስተዳደር ችግሮችን የመፍቻ መንገዶችን በመጠቀም፤ እንዲሁም፣ የስራ አጥነት ችግርን በፈጠራ ስራዎች በመሸፈን አፍሪካን ከግብዓት አቅራቢነት ወደ ከፍተኛ አምራችነት ማሳደግ አለባችሁ፤
- አፍሪካውያን ወጣቶች ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ የዕድገት ራዕዮችን በመቅረጽና ለስኬቱ በመስራት የአህጉሪቱን ዕድገት በማረጋገጥ የዓለምን እይታ መቀየር አለባችሁ፤
- የቀድሞ አባቶችን ራዕይ አውቃችሁ ተግባራዊ ለማድረግ መጣር አለባችሁ። የሚል ሲሆን፤ ከዚህ የምንረዳው አቢይ ጉዳይ ቢኖር፣ የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች ራዕይ ምን ያህል ዘመን ተሻጋሪ እንደ ነበር ነው፣ ምንም እንኳን በየጊዜው በስልጣን ጥመኞች እየተደነቃቀፈ ሳንካ ቢገጥመውም የጊዜ ጉዳይ እንጂ ርቆ የተቀበረ አለመሆኑንና የመሳሰሉትን ያሳየም ነው።

"በ2030 ከአጠቃላዩ የዓለም ወጣት ከፍተኛ ድርሻ የምትይዘው አፍሪካ ትሆናለች። አፍሪካ አሁን የሆነችውን ብቻ ሳይሆን፣ ያላትን ዐቅም አገናዝበው ልትሆን የሚገባትን የሚቀምሩላት ወጣት ልጆቿ ናቸው። ፓንአፍሪካዊነትን በአመራራቸው የገለጡ የትናንት ፈር ቀዳጆች ለዚህ ጽኑ መሠረትን ጥለዋል። አህጉራችሁ ያላትን ዐቅም ተጠቅማ ለሁሉም ዜጎቿ ምቹ እንድትሆን ማስቻል በተለይም ከአፍሪካውያን ወጣት መሪዎች ይጠበቃል። ስለዚህም የተጣለባችሁን ተስፋ እውን እንድታደርጉት አደራ እላለሁ።" የሚለው ይገኝበታል።

በአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ የቀደሞ መሪዎች በፓንአፍሪካኒዝም ዙሪያ የነበራቸው አመለካከትና ሲያራምዱት የነበረው አፍሪካዊ ፍልስፍና ምን እንደ ነበር የተለያዩ አገራት የቀድሞ መሪዎች (የኢትዮጵያ የቀድሞ ፕሬዘዳንት ሙላቱ ተሾመን፣ የጋና የቀድሞው ፕሬዝዳንት ድራማኒ ማህማን ጨምሮ) ለወጣቶቹ ያላቸውን ልምድ አካፍለዋል።

በልምድ ማካፈሉ ወቅት የተለያዩ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን፣ አፍሪካ በቅኝ ግዛት ዘመን ያሳለፈችውን ፈታኝ ጊዜ በማለፍ አሁን ባሉ ተስፋ እና እድሎች መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑ፤ የአፍሪካ ባህላዊ እሴቶችን በማዳበር የራሳችን ሞራልና ማንነት መጠበቅ እንደሚገባ፤ ዛሬ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች የሚያሰራጯቸው ሀሳቦች አፍሪካዊ ማንነታችን እያሳጡን በመሆኑ፤ የዚህ ዘመን ወጣቶች ይንን በመከላከል እና በመጠበቅ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚገባቸው፤ አፍሪካውያን በሰላም ግንበታ፣ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና የተፈጥሮ ሀብትን በበቂ መጠን መጠቀም የነገ ትውልድ መሪዎች አቅም መገንባት የሚያስፈልግ መሆኑ፤ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄዎችን መፈለግ እንደሚገባ (በአምባሳደር ተስፋዬ ይልማ "ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ መቅረቡን ለማወቅ ተችሏል)፤ በተለይም የወጣቶችን አቅም በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀም በፈጠራ የዳበረች አህጉርን ለመገንባት አፍሪካዊያን ዛሬ ነገ ሳይሉ መነሳት ያለባቸው ስለመሆኑ፣ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው።

አፍሪካውያን በህብረት ሲቆሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነታቸው መጠን እንደሚጨምር እና በዚህ ረገድ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ሰፊ እንቅስቃሴ መደረግ እንዳለበት፤ ለሁሉም የፓን አፍሪካኒዝም ፅንሰ ሀሳብን በሚገባ ማዳበር እንደሚገባ (በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ማዕከል ሚኒስትር ዛዲግ አብረሃ "የፓንአፍሪካኒዝም እሳቤ እና ታሪክ" የሚል ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቧል)፤ በኢትዮጵያ ሀሳብ አመንጪነት የተጀመረው ይህ አይነቱ የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባኤን የመሰሉ ጉባኤዎች በስፋት ሊካሄዱ እንደሚገባ፤ በአፍሪካ ለሚፈጠሩ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ እንዲሁም ማህበራዊ ችግሮች ብቸኛው መፍትሔ አፍሪካውያን ችግሮችን የሚፈቱበት መንገድ የራሳቸው አገር በቀል እውቀት ሊሆን እንደሚገባ ፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የአፍሪካ አህጉር የምትወከልበት ስርዓት በድጋሚ መታየት ያለበት መሆኑም በጉባኤው ላይ ከተነሱት መካከል እንደ ነበሩም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ለመሆኑ "የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች" ስንል ምን ማለታችን ነው?

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች" የሚለው የአፍሪካ ወንድማማችነትን የሚያቀነቅነው ንቅናቄ (ፓንአፍሪካኒዝም) መቀንቀን ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ያለውን፤ በተለይም አፍሪካ ከነጭ አገዛዝ ነፃ እየወጣች ከመጣችበት 1950ዎቹ እና 60ዎቹ ወዲህ ያለውን የጊዜ ሰሌዳና የነፃነት እንቅስቃሴን የሚመለከት ሲሆን፤ የዚህ ወቅት የለውጥ ጠንሳሾችና አራማጆችን የሚመለከት አገላለፅ ነው።

ጠንሳሾቹና አራማጆቹ፣ "የዘመናዊት አፍሪካ መስራች" ያልናቸው አባቶች በመሰረቱት በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ በተካሄደው ከመላው አፍሪካ ለተወጣጡ የአፍሪካ ወጣት መሪዎች ጉባኤ ላይ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ እውቅና የተጣቸው ሲሆን፤ እነሱም፡-

አፄ ኃይለሥስላሴ ኢትዮጵያ፣ ንጉስ ሀሰን ሁለተኛ / ሞሮኮ፣ ጁሊየስ ኒሬሬ /ታንዛኒያ፣ አህመድ ሴኩቱሬ /ጊኒ፣ ሊዮፖልድ ሴዳር ሴንጎር /ሴኔጋል፣ ጆሞ ኬንያታ /ኬንያ፣ ጋማል አብድል ናስር/ ግብፅ፣ ክዋሜ ንኩርማህ /ጋና፣ ኬኔት ዴቪድ ካውንዳ /ዛምቢያ፣ ኔልሰን ማንዴላ /ደቡብ አፍሪካ፣ ሮበርት ጋብሬል ሙጋቤ /ዚምባብዌ፣ አቡበከር ታፋዋ ባሌዋ /ናይጀሪያ፣ ሞዲቦ ኬታ /ማሊ፣ ዊሊያም ቲዩብማን /ላይቤሪያ፣ አህመድ ቤን ቤላ /አልጀሪያ፣ ፍሌክሲ ሆፎየት ቦይኒ /አይቮሪኮስት፣ ሳሞራ ማሼል /ሞዛምቢክ ናቸው።

## የሕብረቱ ወቅታዊ ቁመና እና የመስራች አባቶች ራእይ

የወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ ማህማት ሲሆኑ በእሳቸው የሀላፊነት ዘመን በርካታ ችግሮች ተከስተዋል። እየተከሰቱም ነው።

ችግሮቹን ለመፍታትም ህብረቱ ከቀድሞው በተሻለ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ። አንዳንዶቹን፣ በተለይም "አይፈቱም"፣ "የአፍሪካ ሕብረት አይቻለውም" የተባለውን ግጭት (ባለፈው ሳምንት በደቡብ አፍሪካ (ፕሪቶሪያ) በኢፌዴሪ መንግሥት እና በህወሓት መካከል ሲካሄድ የቆየው ውይይትና የተደረሰበት የተኩስ ማቆምና የሰላም ስምምንት ልብ ይሏል) የመሸምገሉ ሁኔታ ተሳክቶላቸው እየተመሰገኑና እየተደነቁ ይገኛሉ። እሳቸው ብቻ አይደሉም፣ አይሰራም የተባለው የአፍሪካን ችግር በአፍሪካዊ መፍትሄም ውጤታማ ሆኖ በመገኘቱ በብዙዎች ዘንድ የሀሳቡ አመጭ የሆኑቱ መስራች አባቶች እየተደነቁና ሀሳባቸውም መሬት እየወረደ ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

የቀድሞ የናይጀሪያ ፕሬዝዳንትና የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ኦሉሴጉን ኦባሳንጆም የቀድሞዎቹን "የዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች"ን በመተካቱና ችግሮችን መፍታቱ ላይ በርትተው በመስራት ምትክነታቸውን እያስመዘገቡ ባሉት ውጤት እያሳዩ ነው።

እንደ አገር ሲታይም፣ ኢትዮጵያ ሁሉ ነገሯን፣ ልክ እንደ ቀድሞዎቹ ኢትዮጵያዊያን መስራች አባቶች ሁሉ፣ ዋና ዋና ችግሮችን በተመለከተ መፍትሄው መምጣት ያለበት ከራሳችን ከአፍሪካዊያን ነው። የአፍሪካዊያንም ችግር መፈታት ያለበት በራሳቸው ነው እንጂ የማንም ጣልቃ ገብነት ሊኖር አይገባም በሚል አቋም ፀንታ ለሕብረቱ ግርማ ሞገስ እየሆነች ትገኛለች።

ከሕዳሴው ግድብ ጀምሮ አሁን ለገጠማት ከፍተኛ ችግር በሙሉ መታየትም ሆነ መዳኘት ያለበት በአፍሪካ ህብረት በኩል ብቻ ነው በሚለው አቋማ በመፅናትና ተፅእኖም በመፍጠር ጉዳዮች ወደ አፍሪካ ሕብረት እያመሩ፤ በዛው በኩልም መፍትሄ እያገኙ፤ ሂደትና የአለምን ትኩረት እየሳበ ይገኛል።

## አጀንዳ 2063 እንደ አንድ የአፍሪካ መስፈንጠሪያ ቦርድ

የአፍሪካ ሕብረት የ50 ዓመት የአንድነት፣ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተገለጸበት አጀንዳ 2063 ዋነኛ ግብ አፍሪካን በመሰረተ ልማት በማስተሳሰር የኢኮኖሚና የፖለቲካ ውህደት መመስረትን፤ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ማጠናከርን ታሳቢ ያደረገውን እቅድ ተግባራዊ በማድረግ በኩል ርብርብ እየተደረገ ሲሆን፣ ይህንን ተግባራዊ በማድረጉም ሆነ የመስራች አባቶችን ራዕይ እውን እንዲሆን በማስቻሉ በኩልም ኢትዮጵያ የመሪነት ሚናዋን እየተጫወተች ትገኛለች።

## በመጨረሻም

አፍሪካ ምንም ሳታጣ ምንም የሌላት አህጉር ሆና ሺዎች አመታትን አሳልፋለች። በኢምፔሪያሊዝም ተደቁሳለች። በእጅ አዙርም ሆነ በግልፅ ቅኝ አገዛዝ እየተገላበጠች አራለች። ተዘርፋለች። አፍሪካዊያን እርስ በእርስ ይጋደሉ ዘንድ በተዘጋጁ ወጥመዶች ውስጥ በመግባት ተጨራርሰዋል ። በ"አፍሪካን መቀራመት" (የጀርመኑ ጉባኤ) የእንስሳ ፍልስፍና ተውጠው በአገራቸው ባይተዋር ሆነው ኑረዋል። ተቆጥሮ አያልቅም። የፓንአፍሪካኒዝም መነሻ ይህ ሁሉ ሲሆን፣ መድረሻውም ከዚህ ሁሉ ቆሻሻ ፅድት ያለች አፍሪካን ማየት ነው። ይህ ደግሞ፣ በአሁኑና መጪዎቹ ትውልዶች እውን እንደ'ሚሆን የአሁኑ የአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ ጥሩ ማሳያ ነውና ያበረታታል፤ ሊበረታታም ይገባል።

ዘላለማዊ ሰላምና እረፍትን ለዘመናዊት አፍሪካ መስራች አባቶች!!!

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ረቡዕ
አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ከፊፋ ዋና ጸሐፊ ጋር መከሩ

ብርሃን ፈይሳ

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በኢትዮጵያ የስራ ጉብኝት ያደረጉትን የፊፋ ዋና ጸሃፊ ፋትማ ሳሙራን በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል፡፡ ዋና ጸሃፊዋ ፋትማም ስምንት መቶ የእግር ኳስ ትጥቆችን እንዳበረከቱ ተገልጿል።

የአለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ተቋም ፊፋ ዋና ጸሃፊ የሆኑት ፋትማ ሳሙራ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት በኢትዮጵያ የስራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የስራ ሃላፊዎች ጋር የተለያዩ ውይይቶችን እንዳደረጉ ተጠቁሟል።

ዋና ጸሐፊዋ በስራ ጉብኝታቸው ወቅት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ተገኝተው ምልከታዎችን ያደረጉ ሲሆን፤ በመጨረሻም የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ጸሃፊዋን ተቀብለው እንዳነጋገሩ ከፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ፕሬዘዳንቷና ዋና ጸሐፊዋ በመከሩበት ወቅት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ እንዲሁም የጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ ባህሩ ጥላሁንም ተገኝተዋል፡፡

በፕሬዘዳንቷ ጽህፈት ቤት በነበረው ውይይት ላይ ዋና ጸሃፊዋ ፋትማ ሳሙራ፣ ድርጅቱ (ፊፋ) በ90ዎቹ በተከሰተው የዓለም መንግስታት የአደረጃጀት ማስተካከያ ወቅት ለስፖርትና ለስነዜጋ የትምህርት አይነቶች የተሰጠውን አነስተኛ ግምት ለማስተካከል በትምህርት ቤቶች የእግር ኳስ ስፖርትን ለማስፋፋት እየጣረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ፕሬዚደንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያና በፊፋ መካከል ጠንካራ ግንኙነት ያለ መሆኑን ገልጸው የእግር ኳስ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ጨምሮ ለሴትና ወንድ ታዳጊ ህጻናት እየተደረገ ላለው ድጋፍ ፊፋን አመስግነዋል፡፡

ዋና ጸሃፊዋ ፋትማ በኳታር ከቀናት በኋላ በሚጀመረው የዓለም ዋንጫ ላይ ፊፋ የሚጠቀምበትና ስማቸው ያረፈበትን ኳስ ለፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ማበርከታቸው ታውቋል። ከዚህ ጎን ለጎንም ዋና ጸሀፊዋ ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት ሁሉ ከ800 በላይ የሚሆኑ ዓለም በዚህ ወቅት እየተጠቀመባቸው ያሉ የመጨረሻ ደረጃ የተለያዩ የእግር ኳስ ትጥቆችን ለኢትዮጵያ አበርክተዋል። ዋና ጸሐፊዋ ያበረከቱት የስፖርት ትጥቅ የእግር ኳስ መጫወቻ ኳስ፣ ጫማ እንዲሁም ማሊያ ያካተተ መሆኑም ታውቋል።

ሴኔጋላዊቷ የፊፋ ዋና ጸሃፊ ባለፈው ዓመትም በፊፋ ስም ለ600 ታዳጊዎች የሚሆን የእግር ኳስ ስፖርት ትጥቅ ለፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ መስጠታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ፕሬዚዳንቷም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በተለያዩ ቀናት በተካሄዱ መርሃ ግብሮች በፊፋ ስም በአዲስ አበባ ከተማ በዝቅተኛ ኑሮ ለሚገኙና እግር ኳስን ለሚያዘወትሩ ታዳጊ ወጣቶች ማበርከታቸው የሚታወስ ነው።



የፊፋ ዋና ጸሃፊ ፋትማ ሳሙራ በኳታር ዓለም ዋንጫ ጨዋታ የሚደረግበት ኳስ ለኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ አበርክተዋል፣

ዋና ጸሐፊዋ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜዎች በኢትዮጵያ የስራ ጉብኝት ማድረጋቸው የሚታወስ ሲሆን ከአመታት በፊትም ከፊፋ ፕሬዝዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ ጋር በመሆን በካፍ የምስረታ በዓልና በጠቅላላ ጉባኤው ላይ በእንግድነት ለመገኘት አዲስ አበባ ተገኝተው ነበር።

በተለይም በዚያን ወቅት ዋና ጸሐፊዋ የፊፋ ክፍለ አህጉራዊ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በአዲስ አበባ በሚቋቋምበት አግባብ ዙሪያ በወቅቱ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ድሪባ ኩማ ጋር በመወያየት ጥረት አድርገዋል። በወቅቱም ፊፋ በአዲስ አበባ ጽህፈት ቤት ከመክፈት በተጨማሪ ተከታታይ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን የማካሄድ ፍላጎት እንዳለው መግለጻቸው አይዘነጋም።



# በጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተተዉ ዕቃዎች ግልጽ የጨረታማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር ግ-20/2015 ጨረታ

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስመጪዎችን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 ወይም/እና አንቀፅ 156 ንዑስ አንቀፅ 4 ወይም/እና አንቀፅ 169 ንዑስ አንቀፅ 2 (በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻሉ ሆኖ) ወይም/እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 168 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ዕቃቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ባለመውሰዳቸው ወይም የጉምሩክ ሕግን በመተላለፋቸው ምክንያት ዕቃዎቹ እንደተተዉ ወይም እንደተወረሱ ተቆጥረዋል፡፡ ስለሆነም የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተተዉ ወይም የተወረሱ ዕቃዎችን በገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ኮሚሽን በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ስለሚወገዱበት ሥርዓት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 167/2012 አንቀጽ 9 መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ማለትም SKD JAC different model Vehicles manufactured year 2012 (ያልተገጣጠመ ተሽከርካሪ) ፣ Bopp Film Plastic Not Printed (ፕላስቲክ መጠቅለያ)፣ Drawer Handle (የድራወር እጀታዎች)፣ Leather Sofa, Tables & Other Furniture (ሶፋ ፣ ጠረጴዛ እና ሌሎችም የቤት ውስጥ ዕቃዎች) ፣ Digital and vernier Caliper (ካሊፓር መለኪያ) ፣ SKD Stainless Steel water tanker (የውሃ ታንከር)፣ Copper Welding Wire (መበየጃ ሽቦ) ፣ natural rubber (የጎማ መስሪያ ጥሬ ዕቃ) ፣ Woven Breathable Women shoes (ቡትስ ጫማ ለሴቶች) እና Polyster Yarn (ክር) በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጫረት የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ የጨረታ ሠነድ እና መመሪያ መግለጫ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ዘወትር ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 6:00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7:00 እስከ ቀኑ 10፡30 እና ዓርብ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5:00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7:30 እስከ ቀኑ 10:30 እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5:30 የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) በመክፈል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ሂሳቦች ቡድን መውሰድ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር በዘርፉ የፀና የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤ ሆኖም ግምታዊ ዋጋቸው ከብር 500,000.00 በታች የሆኑ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ ሳያስፈልግ መወዳደር ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ አሸናፊው እንደታወቀ በ3 (ሦስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፉበት ዋጋ ላይ የሚታሰብላቸው ይሆናል፡፡ ተጫራቾች የሚያስይዙት CPO በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም ETHIOPIAN CUSTOMS COMMISSION MODJO BRANCH OFFICE በሚል ሲሆን የግል ባንክ ከሆነ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቅርንጫፎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሆነ ደግሞ ከአዲስ አበባ፣ አዳማ እና ሞጆ ቅርንጫፎች መዘጋጀት አለበት፡፡ ተሳታፊዎች ዋጋ መሙላት የሚችሉት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው ማህተም ያረፈበት ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ በመግዛት የሚወዳደሩበትን ዕቃ አስቀድሞ ማየት ያለባቸው ሲሆን ዕቃውን ሳያዩ ለሚሞሉት ዋጋ ቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡
5. የግልጽ ጨረታ ተሳታፊ ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃ ለመግዛት የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ፣ የሞሉበት ሠነድ፣ በተራ ቁጥር 2 የተገለፁትን ማስረጃዎች ኮፒ እና ያቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO በኤንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ የጨረታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ8 ተከታታይ ቀናት ጠዋት 4:45 ድረስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል፡፡
6. የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
7. የጨረታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣበት ቀንን ጨምሮ በ8ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4:45 ታሽጐ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 5፡00 ላይ ተጫራቾቹ ወይንም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ በአዘጋጀው ቢሮ ውስጥ ይከፈታል፡፡
8. ማንኛውም በግልጽ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይንም የሌላ ተጫራቾችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም፡፡
9. ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ጨረታውን ለማሸነፍ ሲል መደለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ይወገዳል፡፡ ጨረታው ከተካሄደ በኋላም ቢሆን የጨረታ አሸናፊው ጨረታውን ያሸነፈው በህገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ የጨረታ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡
10. ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤት እና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይችልም፡፡
12. ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡
13. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፋቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለባቸው፡፡ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ያስያዙት ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡ ያሸነፉት ዕቃም በድጋሚ ለጨረታ ሽያጭ ይቀርባል፡፡
14. በተራ ቁጥር 12 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ ዕቃውን ያላነሳ/ያልተረከበ እንደሆነ ለሚቆይበት ለተጨማሪ ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፍላል፤ ሆኖም ዕቃው በ2 (ሁለት) ወራት ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በጨረታ ሽያጭ ይወገዳል፡፡
15. አሸናፊው ተጫራች ዕቃዎችን ለመረከብና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ ራሱ ይሸፍናል።
16. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ የአቀረበውን ዕቃ ብዛት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ሙሉ መብት አለው።
17. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከአገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
18. ለተጨማሪ ማብራሪያ በሥልክ ቁጥር 022-236-9094 ላይ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

# በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት